ንገሬታይ [illegible]
የካቲት 22/4/3/

# መግቢያ

እንደሚነገረው ባለፉት አስርት ዓመታት እጅግ የላቀ ሀይማኖታዊ እንቅስቃሴ የታየው በክርስትና እምነት ተከታዮች ሳይሆን በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ነው። ከክርስትና ሀይማኖት ውጪ እስልምና ሌላው በመልክተኞቹ የጋለ እንቅስቃሴ በፍጥነት በመስፋፋት ላይ ያለ ብቸኛ ሀይማኖት ነው።

የእስልምና ዕድገትና መስፋፋት ዋና አላማውም አለምን በሙሉ ወደዚህ የእስልምና ሀይማኖት ለመመለስ እንደሆነ ግልፅ ነው። እያንዳንዱ ሙስሊሙም ሌላውን ሰው ወደዚህ ሀይማኖት የመጋበዝና ያ ሰው የነብዩ መሀመድን አስተምህሮ እና የእስልምና ስርዓት እንዲከተል ግፊት እንዲያደርግ ይገደዳል። ይህም ሌላውን ሀይማኖት የሚከተልን ሰው ወደ እስልምና ትምህርት የሚደረገው ግብዣ ወይም ጥሪ «ዳዋህ» ይባላል።

የሚያሳዝነው ግን ጥቂት ሙስሊሞች ሁሉም ባይባሉም በዚህ የሀይማኖታዊ ግለት ውስጥ ገብተው ክርስትናንና አስተምህሮውን ለማጥቃት ሲጥሩና እስላምም ከሁሉ የበለጠ ሀይማኖት እንደሆነ አድርገው የሚናገሩ አሉ ይህ ደግሞ ትህትና የጐደለው አካሄድ ነው። ይህ አይነቱ አስተሳሰብና የሌላውን ባህልና ሀይማኖት የመንቀፍ አድራጐት መጨካከንና በህብረተሰብ ዘንድ አለመረጋጋትን ያመጣል። አንድ የማይካድ ነገር ቢኖርም አንዳንድ ስሜታዊ ክርስቲያኖችም በዚህ አይነት ተመሳሳይ ስህተት የሚወድቁ እንዳሉ መታወቁ ነው። እነዚህ ሰዎች የክርስቶስ መንፈስ ያልተላበሱ ስለሆነ የእስልምናን ነብይ የሆኑትንና የሙስሊሙን ባህልና ወግ ሲያቃልሉ ይታያሉ። ይህም ለሙስሊሙ ህዝብ እንግዳ ነገር አይደለም እንዲያውም መሀመድ በህይወት በነበሩበት ዘመን ሳይቀር ስመ ክርስቲያኖች በእስልምና እምነት ላይ ያሾፉ እንደ ነበር ይታወቃል።

> *«ይህን አድራጐት በመቃወም ቁርዓን ሲያስጠነቅቅ አይሁዶችም እና ክርስቲያኖችን ሙስሊሞች ጓደኛ እንዳያደርጓቸው ያዝና ምክንያቱን ደግሞ በሀይማኖት ላይ ማሾፋቸው እንደሆነ ይገልፃል።»* *ሱራቱአል ማኢዳህ (5):51እና57*

ከነእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት በስተቀር ግን ቅዱስ ቁርዓን ስለክርስቲያኖች ቀና የሆነ ነገርን ያስቀምጣል። በእውነት ክርስቶስን ለሚከተሉት ሲናገር ግን ሙስሊሞችን ከሚቀርቡት መካከል ግን «ለመማር የተዘጋጁ» ፣ «አለምን የካዱ» ፣ «ክፋት የሌለባቸው» በማለት ሲያወድሳቸው ይታያል። ሱረቱል - ማኢዳህ (5):82 ተመልከት

> *«አላህም ደግሞ በእውነት ለሚያምኑ ለደቀ መዛሙርት ሀይልን እንደሚሰጣቸው በሱረቱል ሳፍ (61):14 ላይ ያስቀምጠዋል ከዚህ በተጨማሪም አላህ በመጨረሻው*

ቀን አልመሲህ ኢሳን የተከተሉትን ሀይማኖትን ከሚከዱ የበለጠ ወይም የላቁ እንደሚያደርግ ቃል ሲገባ እንመለከታለን::» ሱረቱል ኢምራን (3):55

«ላሀ ርህራሄውንና ምህረቱንም በአልመሲህ ኢሳ ተከታዮች ልብ ውስጥ እንደገለጠም ይናገራል::» ሱረቱል ሀዲድ (57):27

ሙስሊሙን ህዝብ በተመለከተ ባጠፉ ክርስቲያኖች ቦታ በመሆን ስለእነሱ ይቅርታ ለመጠየቅ አታመንታ:: ቁርዓን በሚያስተምረው ሁሉ ባትስማማም ሙስሊሞችን እጅግ ከሚቀርቧቸውና ከሚወዷቸው አልመሲህ ኢሳ ተከታዮች አንዱ እንደሆንክም ሙስሊሙ ይገነዘብሀ:: ቃልና ድርጊትህም ደግሞ አንተን አንድና እውነተኛ አምላክ የሆነውን የአብርሃምን አምላክ እንደምታምን ይመስክሩ:: ለእርሱም እንደምትገዛ አረጋግጥላቸው::

ከልብ በሆነ ፍቅር አንተም ለመማር የተሠጠህ ከአለም ውሸት ነፃ የሆንክ ትሁት አላህንም መርዳት የምትፈልግ በጠላትህም ላይ ድል ለማግኘት በፀጋ የተሞላህ እስከመጨረሻም ለመፅናት የዘጋጀህ ልቡህ በምህረትና ርህራሄ የተሞላ መሆንህን በግልፅ አሳይ:: ይህንን ብታደረግ በእርግጥ በሙስሊሞች ዘንድ በልባቸው የምትገባበት በር ይከፈትልሃል::

ይህንን ያህል ካልን በዚች ፁሑፍ ውስጥ ማረጋገጥ የሚገባን መልዕክቷ የእስልምና እምነት ለመቃወምና ለማቃለል የተዘጋጀች አለመሆኗን ነው:: ዓላማዋም እንደ ዋቢ መፅሐፍ በመጠቀም ለክርክርና ለማሳማንም አይደለም አንተም አስታውስ እንደ እውነተኛ የጌታ ክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ የቃሉን ማስጠንቀቂያ ለመከተል ጠንቃቃ ሁን እንዲህ ይላል እና:

> «ከማይረባ ትርጉም የለሽ ከሆነ ክርክር ራቅ ምክንያቱም እነዚህ ጠብን የሚያስከትሉ ናቸው:: የጌታም አገልጋይ ሊጣላ አይገባውም ይልቁን ለሠው ሁሉ ገር ለማስተማር ብቃት ያለው ትዕግስተኛ መሆን ይገባዋል:: እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ እግዚአብሔር ንስሀን እንደሚሠጣቸው ተስፋ በማድረግ የሚቃወሙትን በየዋህነት የማያቃና መሆን ይኖርበታል::» 2ጢሞ2:23-26

እንዲሁም በማንም ላይ ክፉ እንዳይናገሩ ሰላማውያን እንደሆኑ ለሰዎችም ሁሉ ከልብ የመነጨ ትህትና እንዲያሳዩ አስገንዝባቸው:: ቲቶ 3:1:2

ይህች ትንሽ ፅሑፍ ብዙ አመታት ልምድን ከሙስሊሙ ህብረተሰብ ጋር ከ15 ዓመታት በላይ አንድ ላይ የኖሩ ወገኖች ሀሳብና የተለያዩ ፀሐፊዎችም ሀሳብ የተወሰዱ

መልዕክቶች ያዘለች ናት። እናም የሚቀጥሉት ገፆች በክርስቲያኖች ላይ እምነታቸውን ለመገዳትና ሌላ ጥርጥርን ለማምጣት የተካኑ ተከራካሪ ሙስሊሞችን ተግዳሮት ለመከላከል የሚረዱ ሀሳቦችን ይዘዋል። ይሁን እንጂ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ከሁሉም የተሻለ መልስ ለመስጠት ክርስትናን በህይወት ኖሮ ማሳየት ነው። እያንዳንዱ ጥረት እውነተኛ አማኝ የሆነው ክርስቲያን የሚያደርገው ነገር ከሙስሊሞች ጋር ጓደኝነት መፍጠርና ወንድማማች መከባበር መመስረት ነው። የሙስሊም ጓደኛ መመስረት የትህትና ኑሮ ማሳየት በየቀኑ የክርስቶስን ፍቅር መኖር የጠረጠረውን ልብ የሚያቃልጥ እና ታላላቅ እውነቶችን መግለፅ መቻል እንዴት የበለጠ ነገር ነው።

በጓደኝነት ወንድማዊ መከበበር ባለው ግንኙነት አማከኝነት ይህች ፅሑፍ ምላሾችን በመስጠት እውነትን ለሚፈልግ ሙስሊም እጅግ ጠቀሚ እንደሆነች ይታመናል። እንዲህ ያለው ግልፅ ውይይት በእርግጥ ሙስሊሙን ባልደረባ መጽሐፍ ቅዱስን እና በውስጡ ያለውን እውነት ለማወቅ ትልቅ ጥማት እንዲፈጠርበት እናም በመጨረሻም እውነትን እና የድህነት መንገድ የሆነውን መሲሁን ኢሳን ለማወቅ መሻቱን እጅግ ይጨምራል።

እውነተኛ የኢየሱስ ተከታዩች ሹመታቸው ክንድን ለማሳየትና የቃላት ጦርነት ለማንሳት አይደለም። በምትኩ የተጠሩትንና የተሾሙትን አለማዊ ግብ ትተው የወንጌልን መልዕክት ለአለም ሁሉ ለማድረስ ነው። እንደ እግዚአብሔር አገልጋዩች ተልዕኮአቸው የክርስቶስን ፍቅር ለመግለፅ እና የኃጢያት ይቅርታ በስሙ እንደሚገኝ መንገር ነው። በተጨማሪም የክርስቶስ አምባሳደሮች በመሆን የዕርቅን ቃል መስበክ ሰዎች ከፈጣሪያቸውና እርስ በርሳቸው እንዲታረቁ የምንናገር መሆን ይጠበቅብናል። ይህን የተቀደሰ ተግባር ጌታ እግዚአብሔር ይባርክ።

# የሙስሊሙ አስተምህሮዎች

## 1. ቅዱስ ቁርአን የመጣው መፅሐፍ ቅዱስን ለመተከት ነው

ብዙ ሙስሊሞች ቁርአን የመጣው የአይሁዶችን እና ክርስቲያን ቅዱስ መፅሐፍ ለመተካት ነው ፣ ምክንያቱ መፅሐፍ ቅዱስ ስህተት ያዘለ የተለወጠ እና ጊዜው ያለፈበት እንደገናም የመጀመሪያው የጠፋ ነው ይላሉ። ይሁን እንጂ ቅዱስ ቁርአን ግን ይሕንን ሀሳብ አልያዘም እንዲያውም ቅዱስ ቁርአን በግልፅ ያስቀመጠው ቁርአን የተላከው የበፊቶችን መገለጦች ለማረጋገጥ እነደሆነ ነው። በሚከተሉት ማስረጃዎች ቁርአን የመጣው ለማስተካከል ፣ ለመተካት ለማስወገድ ፣ ለመለወጥ ወይም ዋጋ ለመሳጣት ሳይሆን ለማረጋገጥ ነው የመጣው።

*ከእናንተ ጋር ያለውን /መጽሐፍ/ የሚያረጋግጥ ሆኖ ባወረድኩትም /ቁርዓን/ እመኑ::     አል-በቀራህ /2/:41*

*ከነሱም ጋር ያለውን /መጽሐፍ/ አረጋጋጭ የሆነ መጽሐፍ ከአላህ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ::     አል በቀራህ /2/:89*

*እርሱ ከእነሱ ጋር ላለው /መጽሐፍ/ አረጋጋጭ የሆነ መልክተኛ /መሀመድን/ ከአላህ ዘንድ::     አል-በቀራህ/2/:101*

*ከበፊቱም /ከቁረአን/ የሙሴ መፅሐፍ መሪና ፀጋ ሲሆን አለ ይህም /ቁርአን/ እነዚያን የበደሉትን ሊያስፈራራ በዐረብኛ ቋንቋ ሲሆን /የፊቶቹን መጽሕፍት/ አረጋጋጭ መፅሐፍ ነው::     አል ቀሕፍ/46/:12*

*ይህም ያወረድነው /ቁርአን/ የሆነ ብሩክ ያንንም በፊቱ የነበረውን /መጽሐፍ/ አረጋጋጭ መፅሐፍ ነው::     አል-አልዓም/6/:92*

*ወደ አንተም /መሐመድ/ መጽሐፍን አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባቂ ሲሆን በእውነት አወረድን::     አል-ማኢዳን /5/:48*

እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተያዙት መገለጦች አስፈላጊነታቸው ለምንድን ነው? ለምን ቁርአን ለማረጋገጥና ለመከላከል መጣ? ራሱ ቅዱስ ቁርአን መልስ ይሠጠናል:: ያለፉት የቃል መገለጦች የመጡት የሰውን ልጅ ለማስጠንቀቅ ለዕውቀት ፣ ለምህረት ፣ ለመምራት እናም ብርሃን እንዲሆን ይህም ብርሃን በእርግጥም ብቸኛ ብርሃን አለምን ከጨለማው ሐጢያት ወደ ክብር ወዳለው ደህንነትና የዘላለም ህይወት የሚያደርስ ነው:: ቅዱስ ቁርአን የሚሠጠውን ምስክርነት እንመልከት::

*ከእርሱ በፊት ያሉትን መጽሐፍት የሚያረጋግጥ ሲሆን መጽሐፍን /ቁርአንን/ ባንተ ላይ ከፋፍሎ በዕውነት አወረደ ተውራትንና እንጂልንም አውርዷል::
አሊ-ዒምራን /3/:3*

*እኛም ተውራትን በውስጥም መምሪያና ብርሃን ያለበት ስትሆን አወረድን:: አል-ማኢዳህ /5/:46*

*ለሰዎች የልብ ብርሃን መሪም እውነትም ሲሆን ይገሠፁ ዘንድ ለሙሴ መጽሐፍን /ቁርአን/ በእርግጥ ሰጠነው::     አል-ቀሰስ/28/:43*

በድጋሚ ለሙስሊሙ እጅግ አስፈላጊው እና ሊያውቀው የሚገባው ነገር እነዚህ መጽሐፍት ቁርአን የመሠከረላቸው ራሳቸው አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙት ናቸው

እነዚህ መጻሕፍት ከእግዚአብሔር የተሠጡ ተአምራቶች ሲሆኑ ሊታመኑ የሚገባቸው ናቸው:: በዚህ ላይ ቁርአን በግልፅ ሲናገር: -

*/ከቁርዓን/ በፊት ለሰዎች መሪ አድርጐ /አወረዳቸው/ ፍርቃንንም አወረደው እነዚያ የአላህ ታአምራቶች የካዱ ለእነርሱ ከባድ ቅጣት አለባቸው:: ኢሊ-ኢምራን (3):4*

*ወደነዚህ በመጽሐፍ በዚያም መልእክተኞችንን በርሱ በላክንበት ወዳስተባበሉት /አታይምን/ ወደፊትም ያውቃሉ እነዚህ ሰዎች ሰንሰለቶቻቸው በአንገቶቻቸው ላይ በተደረጉ ጊዜ /በርሷ/ ይጐተታሉ:: በገሃነም ውስጥ /ይጐተታሉ/ ከዚያም በእሳት ውስጥ ይማገዳሉ:: አል መአሚን/40/:70-72*

## 2. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተለውጧል

*በየትኛውም ክፍል ቁርአን የክርስቲያኖችና የአይሁድ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል መለወጡን አይናገርም:: የሚነቅፈው የመጽሐፍ ሰዎች መልዕክቱን በራሳቸው ቃል ሲተረጉሙትና ሌላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲሰውሩት ነው:: ከነሱም እርሱ ከመፅሐፍ ያይደለ ሲሆን ከመፅሐፍ መሆኑን እንድታስቡ በመፅሐፍ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ:: አል-ኢምራን/3/:78*

እነዚያ የሚናገሩ ሰዎች የመጽሐፍ መልዕክት ለመለወጡ በቂ ማስረጃ መስጠት ይኖርባቸዋል:: እጅግ የተለመደው ሙከራ የበርናባስ ወንጌል የተባለውን አባዝቶ በማሠራጨት ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ጥረት አለፋሪነቱ ከቁርአን ጋር መጋጨቱ ተረጋግጧል:: የተለያዩ ፅሁፎች ቢኖሩም ሆንብሎ በመፅሐፍ ቅዱስ የተደረገ ለውጥ የለም:: መሰረታዊ አስተምህሮን የሚቀይር ምንም ለውጥ አልተደረገም:: የምንባብ ልዩነት ደግሞ በቁርአንም እንደሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስም ይገኛል:: ለምሳሌ የሱፍ አሊ የጻፈው ቅዱስ ቁርአን መግቢያ ላይ ልዩነቶች ይታያሉ::

እንግዲህ የመፅሀፍ ቅዱስ መለወጥ ከግምት ውስጥ ከገባ የሚከተሉን ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀሩም::

### ጥያቄ ሀ. የመፅሀፍ ቅዱስን ጥቅስ ማን ለወጠው?

አይሁዶችና ክርስቲያኖች በመተባበር መጽሐፍ ቅዱስን ለወጡት ይህም ደግሞ የእስልምናን ስርጭት ለማገድ ነው ተብሎ ይነገራል:: ሆኖም የማይመስልበት ምክንያት አይሁዶችና ክርስቲያኖች ሰፊ ልዩነቱ ያላቸው መሆኑ ነው::

እነርሱ መፅሐፍን የሚያነቡ ሲሆኑ አይሁዶቹ ክርስቲያኖች በምንም ላይ አይደሉም አሉ። ክርስቲያችም አይሁዶችም በምንም ላይ አይደሉም አሉ። ኢል በቀራህ (2):113

የመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅስና የክርስትና መሠረት አስተምህሮ ቢለወጥ ኖሮ በርግጥ የሚቃወም ሰው አንድ እንኳን አይጠፋም ምክንያቱም ብዙ ቡድኖች በአይሁድ እና በክርስትና እምነት ውስጥ ስለሚገኙ ነው። እንደገናም በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደዚህ ያለ መሆኑን የሚገልፅ ነገር የለም። መግባባት ያልተቻለውና መካሰስ የመጣው የመፅሀፍ ቅዱሰ ጥቅስ የስህተት ትርጉም ተሠጥቶታል በማለት እንጅ በመለወጥ አይደለም።

ኢየሱስ አይሁዶችን ጥቅሶችን ለወጣችሁ በማለት አልነቀፋቸውም እንዲያውም ትኩረታቸውም ወደነዚያው መጽሀፍ ቅዱስ እንዲሆን ነው ያስተማራቸው። የጥቅስ ለውጥ ቢኖር ኢየሱስ ያጋልጣቸው ነበር። በመሀመድ ዘመነ ህይወት እውነተኛ ክርስቲያን ከሚባሉት መካከል የነበሩት አቢሲኒያ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር በነበራቸው ባልንጀራነት ምክንያት እንደዚያ ያለ ስህተት ቢኖር ያጋልጡ ነበር።

*እነዚያንም እኛ ክርስቲያኖች ነን ያሉትን ለነዚያ ለአመኑት በወዳጅነት በእርግጥ ይበልጥ የቀረቧቸው ሆነው ታገኛለህ . . . . እነርሱም የማይኮሩ በመሆናቸው ነው። አል ማኢዳህ (5) 82*

## ጥያቄ ለ. መቼ ነበር የመጽሀፍ ቅዱስ የተለወጠው?

መጽሀፍ ቅዱስ በእውነት ተለውጦ ቢሆን ይህንንም መሀመድ ከመሞታቸው በፊት አይተው ቢሆን ኖሮ የሚከተሉትን ትምህርቶች በቁርዓን አያስተምሩም ነበር።

*በአላህና ወደኛ በተወረደው /ቁርዓን/ ወደ ኢብራሒምም ወደ ኢስማኢልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቆብና ወደ ነገዶቹ በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አምንን እኛም ለእርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ። አል-ቢቀራህ (2): 136*

*እናንተ የመፅሀፍ ባለቤቶች ሆይ ተውራትንና ኢንጅልን ከጌታችሁም ወደናንተ የተወረደውን እስከምታቆሙ (እስከምትሠሩባቸው) ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው። አል-ማኢዳህ (2):68*

*የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ። አል ማኢዳ (5):47*

*በፊለጎቻቸው (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርያምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከትለን ኢንጅልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያላቸውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲሆን ሰጠነው::       አልመኢዳህ (5): 46*

*ወደ አንተም (መሀመድ) ከወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሀፍን የሚያነቡትን (የመፅሀፍን ሰዎች) ጠይቁ:: ዮኑስ (10): 94*

*ከነሱም ጋር ያለውን (መጽሐፍ) አረጋጋጭ የሆነ መፅሐፍ (ቁርአን) ከአላህ ዘንድ አረጋጋጭ እውነተኛ ሲሆን ይክዳሉ . . . እነርሱ ጋርም ላለው (መጽሐፍ) አረጋጋጭ የሆነ መልክተኛ ከአላህ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ . . . አል በቁራህ (2):89፣91፣101*

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጥቅሶች ውስጥ ሌሎችንም ጨምሮ የሚደጋገመው ሀረግ አረጋጋጭ የሆነ የሚል ነው:: እነዚህ ጥቅሶች የሚያስተምሩት ቁርአን የመጣው ቀድሞ የመጣውን መፅሀፍ ለማስረገጥ እንጅ ለማረም ለመተካት አይደለም:: በየትኛውም የቁርዓን ክፍል የሚያሳየው ቁርዓን የመጣው አንድን እምነት የሚከተሉ ሰዎችን ቅዱስ መጽሀፋቸውን እንዳያበላሹ እንዳይለወጡ ወይም እንዳይሰውሩ ለማስጠንቀቅ አይደለም::

መሀመድ ከሞቱ በኃላም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተለውጧል ብሎ ለማመን የማይመስል ነገር የሚሆንበት ምክንያት እንደሚከተለው ነው::

በ600 ዓ.ም. ክርስትና በእስያ ፣ አፍሪካና አውሮፓ ተስፋፍቶ ነበር:: በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ አለም አቀፍ የሆነ ስብሰባ አልተደረገም::

የመጽሀፍት ቅጅዎች እስከ አሁን ድረስ የአራተኛ እና አምስተኛው መቶ አሉ እነዚህ ቅጅዎች አሁን ካሉ ቅጅዎች ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው::

## ጥያቄ ሐ. እንዴት ተለወጠ?

*ይሁዲነትና ክርስትና በአለም ላይ ከተስፋፋ በኃላ ቅዱስ መጻህፍትን ቅጅዎችና የተለያዩ ጽሁፎችን ከቤተክርስቲያን ፣ ከምኩራብ ፣ ከቤተመፃህፍት ፣ ከትምህርት ቤቶች ፣ ከቤቶች ሁሉ ሰብስቦ መለወጥ እናም እንደገና በቦታቸው መመለስ እንደማይቻል በእርግጥ የታወቀ ነው:: ቅዱስ ቁርአን እራሱ አስረግጦ የሚናገረው ይኸንኑ ነው:: የጌታህን ቃላት እውነተኛና ትክክለኛ ስትሆን ተፈፀመች ለቃላቱ ለዋጭ የለም::    አል - አንአም (6) : 115*

*የአላህ ቃል መለወጥ የለትም:: ዮኑስ (10): 64*

እናም ሙስሊሞች እነዚህ የተጠቀሱትን የሚያምኑ እና አላህም ቁርአንን መጠበቅ ከቻለ ከቁርአን በፊት የነበሩትን ቅዱስ መፃሕፍትም ሊጠብቅ እንደሚችል ማመን አስፈላጊ ነው።

## 3. የመሀመድ ስም ከመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ተወግዷል

ብዙ ሙስሊሞች የመጽሀፍ ቅዱስን ዋጋ ለማሳጣት ሲሞክሩ ይታያሉ ምክንያቱም በውስጡ አንዴም የመሀመድን ስም ባለመጥቀሱ ነው። የመሀመድን ስም በአይሁዶችና በክርስትያኖች ቅዱስ መፀሀፍት ለማየት የሚፈልጉበት ምክንያቱ በእነርሱ መፅሀፍ በቁርአን ውስጥ በሁለት ቦታዎች ባሉት ጥቅሶች የተነሳ ነው።

*የመርያም ልጅ ኢሳም የእስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋገጥና ከኔ በኃላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አህመድ በሆነው የማበስር ሲሆን ወደናንተ የአላህ መልዕክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። አል ሶፍ (61)፡ 6*

*ለነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንደፍ ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የሆነውን መልክተኛ (መሀመድ) የሚከተሉ ለሆኑት (በእርግጥ እድፋታለሁ)በበጎ ስራ ያዛቸዋል ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል። አል አዕራፍ (7)፡157*

እጅግ የተመራመሩ ሙስሊሞች ካደረጉት ጥናት እንደተረዱት በመፅሀፍ ቅዱስ ቅጅ ውስጥ ከመሀመድ ዘመን በፊትና በኃላ ባሉት ቅጅዎች ልዩነት አለመኖሩን ነው። ስለዚህ መፅሀፍ ቅዱስ የተለወጠው የመሀመድን ስም ለማስወገድ ነው። የሚለው ክስ መሰረት የሌለውና እውነተኛ ያልሆነ ነው። ይሁን እንጂ ሙስሊሞች እስካሁንም ሀሰባቸው ሳይለውጡ የመሀመድ ስም በመፀሀፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መሀመድ በግልፅ የሚናገር እናገኛ ለን ይላሉ። በዚህ ምክንያት የመሀመድ ነብይ መሆን እና ለሰው ሁሉ ተልእኮ እንዳላቸው ሙስሊሞች ይገልፃሉ።

በዚሁ መሰረት ክርስቲያኖች ለማሳመን ይጣጣራሉ ክርስቲያኖች መሀመድን እና እስልምናን እንዲከተሉም ለማሳመን ይጥራሉ።

ቁርአናቸውን በማንተራስ ኢየሱስ የሰጠው የተስፋ ቃል ከእርሱ በኃላ የሚመጣው መሀመድ እንደሆነ ብዙዎች ሙስሊሞች መጽሀፍ ቅዱስን በማሰስ በወንጌል ዮሐንስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነገረውን ለመሀመድ ነው በማለት ይደመድማሉ። ለምሳሌ በዩሐንስ ወንጌል 14:16:15:26 እና 16:7 መጥቀስ ይቻላል። የመጀመሪያው የግሪክ ቃል «ጰራቅሊጦስ» የሚለው ትርጉሙ «አፅናኝ» ፣ ጠበቃ «አማካሪ» ተብሎ በእንጊሊዝኛ

ይፈታል። ጥቂት የሙስሊም ፀሀፊዎች የመጀመሪያው የግሪክ ቃል በስህተት የተፃፈ ነው በማለት ይከራከራሉ። ከመጀመሪያው ቃል «ጰራቅለጦስ» የሚል ነው ይህም ደግሞ ትርጉሙ አህመድ ከሚለው ስም ጋር ይቀራረባል ይኸም «ምስጋና ይገባል» ማለት ነው ይላሉ።

ሆኖም አህመድ የሚለው ቃልና መሀመድ የሚለው ቃል በሁለቱ መካከል ልዩነት መኖሩ ግልፅ ነው። መሀመድ የሚለው ትክክለኛ ስም ሲሆን «አህመድ» የሚለው ግን ቅድል ነው። «መሀመድ» አንድ ምስጋና የሚገባው» ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ «አህመድ» ምስጋና ይገባል ማለት ይሆናል። አህመድ የሚለው ስም ከመሀመድ ዘመን በፊት የተለመደ ስም እንዳልነበር ይታመናል። ስለዚህም በቁርዓን ውስጥ አንድም ቦታ ውስጥ የእስልምና ነብይ አህመድ ነው የሚል ቃል አልተፃፈም። በሞትኩ ትክክለኛውን ስም መሀመድ የሚለውን እናገኛለን።

በዩሐንስ ወንጌል ክፍል የተፃፈው «ጰራቅሊጦስ» የሚገልፀው የእውነት መንፈስ አለም የማያውቀው ሆኖም በአማኞች ህይወት ውስጥ የሚኖር ስለ ኢየሱስም የሚመሰክር «አፅናኝ ፣ ጠበቃ እና «አማካሪ» ተብሎ የተፃፈው ነው። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱም የነገራቸው ስለዚሁ ስለ እውነት መንፈስ ነበር።

> *ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌም በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ እስከምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ። ሐዋ 1:8*

ከኢየሱስ ሞት በኃላ ሃምሳ ቀናት ቆይቶ ስለመንፈስ ቅዱስ ለደቀ መዛሙርት ተገብቶ የነበረው ተስፋ ቃል ተሰጣቸው። በበዓለ ሀምሳ ዕለት በአስደናቂ መንገድ ተከናወነ። ይህንን ታላቅ ክንውን ጴጥሮስ ሲገልፅ እንዲህ ብሎ አስረዳ።

> *ይህን ኢየሱስ እግዚአብሔር ከሞት አስነሳው እኛም ሁላችን ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን። ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ካለ በኃላ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ከአብ ተቀብሎ አሁን የምትሰሙትን የምታዩትን አፈሰሰው። ሐዋ 2:32-33*

ከላይ እንደተጠቀሰው «ጰራቅሊጦስ» የሚለው ቃል ለመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ግልፅ ነው። ሰውንም ፈጽሞ አያመለክትም። ከዚህም በላይ «ጰራቅሊጦስ» የሚመጣው ኢየሱስ እንደገባው የተስፋ ቃል ደቀመዛሙርቱ በህይወት እያሉ ነበር። መሀመድ ግን የመጣው 500 አመታት ካለፉ በኃላ ነበር።

ሙስሊሞች የብሉይ ኪዳንን መፅሀፍ በደንብ አድርገው መርምረዋል ፣ በተለይም የሙሴን ህግ መፅሐፍት ካጠኑ በኃላ ስለመሀመድ የተፃፈ ነው ብለው በብዛት ያመኑባቸውን ከውስጡ ነጥለው በማውጣት ለማስረጃነት ይጠቀሙበታል:: ለምሳሌ በዘዳግም 18:15 እና 18 ያለውን ይጠቅሳሉ::

አምላክህ እግዚአብሔር ከገዛ ወንድሞችህ መካከል እንደ እኔ ያለ ነብይ ያስነሳልሀል እርሱን አድምጥ . . . ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነብይ አስነሳላቸዋለሁ:: ቃሌን በአፍ አደርጋለሁ የማዘውንም ሁሉ ይነግራቸዋል::

ብዙ ሙስሊሞችም የሚገልፁት ያ ከሙሴ በኃላ የሚነሳው ነቢይ ሙሴን የሚመስለው ነቢይ መሀመድ ነው በማለት ነው::

## 3. መሀመድ እንደ ሙሴ ነብይ ነበሩ

*ከወንድሞቻቸው መሀመል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሳላቸዋለሁ ቃሌን በአፌ አደርጋለሁ የማዘውንም ሁሉ ይነግራቸዋል:: ዘዳ 18:18*

ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ሙስሊሞች የሚሉት ይህ የተነገረው ለእስራኤል ሕዝብ ለይስሀቅ ዘር ነው ሆኖም ከወንድሞቻቸው መካከል የሚለው የአስማኤልን ዘር ነው ምክንያቱም እስማኤል ይስሀቅ ወንድም ስለሆነ ነው:: ስለዚህ በሚያቀርቡት ማስረጃ «እንደ ሙሴ» የሚለው ትንቢት የሚያመለክተው መሀመድን ነው:: መሀመድ ብቸኛው ታላቅ ነቢይ ዘሩ ከእስማኤል ስለሆነ እናም ልክ እንደ ሙሴ የአላህን ህግ በማስቀመጥ ታምራት በማድረግ አሳየ ይላሉ::

በመጀመሪያ «ከወንድሞቻቸው መካከል» የሚለውን እንመልከት:: እግዚአብሔር ለእስራኤል ንጉስን እንዲመርጡ ሲያዛቸው ያላቸውን እንመልከት ስለተጠቀሰው ሀረግ የበለጠ መረዳት እንችላለን:: ዘዳ 17:14-15 የሚለውን ተመልከት

አምላክህ እግዚአብሔር ወደ ሚሰጥህ ምድር ስትገባ . . . .» በዙሪያዬ እንዳሉት አህዛብ ሁሉ እኔም በላዬ ላይ ንጉስ ላንግስ ብትል እግዚአብሔር አምላክህ የሚመርጠውን ንጉስ በላይህ ታነግሳለህ ከገዛ ወንድሞችህ መካከል እንጂ እስራኤላዊ ወንድም ያልሆነው ባእድ በላይህ አታንግስ::

በእርግጥ የጥንቱን የመሀል ምስራቅ ልማድ የሚያውቅ ሙስሊም እስራኤላውያን ለራሳቸው የሚሆን ንጉስ ከእስማኤል ዘር እንደማይመርጡ ያውቃል:: በተጨማሪም:: «ከወንድቻቸው መካከል» የሚለው ሀረግ በግልፅ የሚያሳየው የእስራኤላዊ ወንድምን ነው::

በሁለተኛ ደረጃ መሀመድን ከሙሴ ጋር ለማነፃፀር ዘዳ 34:10-12 ያለውን ማንበብ ተገቢ ነወ የሆነ ዝርዝር ይዟል የሚመጣውምን ነቢይ ሁኔታ ያሳያል::

እግዚአብሔር ፊት ለፊት ያወቀው እንደሙሴ ያለ ነብይ ከዚያ ወዲህ በእስራኤል አልተነሳም:: እግዚአብሔር ልኮት እነዚያ ታምራዊ ምልክቶችና ድንቆች ሁሉ በግብጽ በፈርኦን በሹማምንቱና በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንዲያደርግ የላከውን ያደረገ ማንም ሰው አልነበረም:: ሙሴ በእስራኤል ሁሉ ፊት ያሳየውን ታላቅ ሀይል ያሳየ ወይም ያደረገውን አስፈሪ ተግባር የፈፀመ ማንም ሰው የለም::

ከነዚህ ቅዱስ ቃላት የምንመለከተው: -

1. ሙሴ እስራኤላዊ ነበር
2. በእግዚአብሔር «ፊት ለፊት» የሚያውቀው ነበር ይህም ቀጥታ ይናገረው ነበር
3. ታላላቅ ተአምራቶች ያደረገ ነው

ሙስሊሞች እንግዲህ የዘዳ 18:18 ትንቢት ፍፃሜ መሀመድ ናቸው ይላሉ:: ይሁን እንጅ ክርስቲያኖች ደግሞ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ከመሲሁ ኢየሱስ ውጪ ማንም ሊሆን አይችልም በማለት ምክንያታቸውን በሚከተለው ንፅፅር መሰረት ያቀርባሉ::

| ሙሴ | ኢየሱስ | መሀመድ |
|---|---|---|
| ከእስራኤላውያ መካከል የሆነ ነብይ | ከእስራኤላውያን መካከል የሆኑ ነቢይ አይሁድ ነገድ (ማቴ:1:3፣ ሉቃ 3:33) | ከአረቦች መካከል የሆነ ነቢይ (ሱራ 46:12:36:6:34:43:44) |
| ከእግዚአብሔር ቃል /መልዕክት/ በቀጥታ ተቀበለ ሱራ 4:164: ዘፀ 33:11 | ከእግዚአብሔር ቃል /መልዕክትን/ በቀጥታ ተቀበለ (ዮሐ 12:49፣50፣14፣10) | በመላእክ ገብርኤል አማካኝነት ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ተቀበለ (ሱራ 2:97) |
| ተዓምራትን አድርጓል (ሱራ 2:50 ባህር ሱራ 2:57 መና) | ተዓምራትን አድርጓል (ሱራ 3:49፣ ማቴ 8:27 ዮሐ 5:11-14) | ተዓምራትን አላደረገም (ሰራ 6:37፣ ሱራ 28:48) |

ከላይ ካየናቸው በተጨማሪ አዲስ ኪዳን የሚያረጋግጠው በዘዳግም 18:18 የተተነበየው ቃል ፍፃሜ ያገኘው በመሲሁ ኢየሱስ ነው በማለት ነው። ሐዋ 3:17-26 በተለይ ቁጥር 22 በግልፅ ስያስቀምጠው።

ሙሴም እንዲህ እንዲህ ብሏል ጌታ አምላካችሁ ከእናንተው መካከል እንደ እኔ ያለ ነብይ ያስነሳላችኋል።

በመዝጊያው ላይ አል-ቀስስ የሚለውን ልብ ይሏል።

*እውነቱም ከእኛ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ ለሙሴ የተሰጠው ብጤ አይሰጠውም ኖሯልን? አሉ አልቀሰስ 28:48*

ስለዚህ ቁርዓን ራሱ ሲያረጋግጥ መሀመድ እንደ ሙሴ ያለ ነብይ እንዳልሆነ መቀበል አያዳግትም።

4. አብርሃም ለመሰዋት የነበረው እስማኤልን ነው ይህም እስልምናን ለወቃወም ብዙ ሙስሞች የሚከራከሩበት እና መጽሀፍ ቅዱስም ተለውጧል የሚሉበት ምክንያት ለአብርሃም የመጣው ልጅ የመሰዋት መለኮታዊ ትዕዛዝ ዝርዝር ታሪክ ነው። ብዙ ሙስሞችም የሚጋተሩት የሚሰዋው ልጅ ኢስማኤል ነው በማለት ነው። መጽሀፍ ቅዱስ ግን የሚያስረግጠው ልጁ ይስሀቅ እንደሆነ ነው። (ዘዳ 22:9 ፣ ዕብ 11:17 ፣ የዕብ 2:21)

በቁርዓንም አንድ ክፍል ብቻ ከዚህ ታሪክ ጋር የሚቀራረብ ታሪክ ሲኖር የሚጀምረውም አብርሃም በሚያቀርበው ጥያቄ ነበር።

ጌታዬ ሆይ ከመልካሞቹ የሆነን (ልጅ) ስጠኝ። ታጋሽ በሆነ ወጣት ልጅም (ምስራች) አበሰርነው። ከርሱ ጋርም ለሥራ በደረሰ ጊዜ ልጄ ሆይ እኔ በሕልሜ እኔ የማርድህ ሆኜ አያለሁ ተመልከትም ምን ታያታህ? አለው አባቴ ሆይ የታዘዝከውን ስራ አላህ ቢሻ ከተጋሾቹ ሆኜ ታገኘኛለህ አለ። ሁለቱም ትዕዛዙን በተቀበሉና በግንባሩም ጐን ላይ በጣለው ጊዜ (የሆነው ሆነ)። ጠራነውም (አልነው) አብራሂም ሆይ ራዕይቱን በእውነቱ አረጋገጥክ እኛ እንደዚሁ መልካም ሰሪዎችን እንመነዳለን /እንሸልማለን/ ይህ እርሱ በእውነት ግልፅ ፈተና ነው። በታላቅም ዕርድም /መስዋዕት/ ተቤዠነው። አል ሳፍፋት /37/:100-107

በዚህ ክፍል ውስጥ ያለውን በጥንቃቄ ይመለከቷል። ይህ ክፍል ብቸኛ ስለ መስዋዕት የሚናገር ክፍል ሲሆን ለመስዋዕት የቀረበው ልጅ ደግሞ ስሙ ፊፅሞ

አልተጠቀሰም:: ይኸ የሚሳየው በተለይ መንገድ ከመግለፁ አስቀድሞ የምስራች የተነገረለት ልጅ መሆኑ ነው:: አንድ ሰው በጥንቃቄ ቁርአንን በሙሉ ቢመረምር ፈፅሞ አንድ ቦታ እንኳ ስለ እስማኤል መወለድ አልተጠቀሰም:: በእርግጥ ስለ እስማኢልም የተባለው ጥቂት ነገር ነው:: ፈፅሞም ስለ እናቱም ስለ ልጆቹም አንዳች ነገር አልተገለፀም:: ስለእስማኤል እናት አጋር መሆን እና አስራ ሁለት ልጆች እንዳሉትም የሚገልፀው ግን መፅሀፍ ቅዱስ ብቻ ነው (ዘፃ 25:12-17):: በቁርዓን የተፃፈው የምስራች መለስ ብለን ብንመለከት ግን ስለ ኢሳሀቅ እና እናቱ ሳራ የምናነበውን ክፍል እናገኛለን::

*የተከበሩት የኢብራሂም እንግዶች ወሬ መጥቶልሀልን? በርሱ ላይ በገቡና ሰላም ባሉ ጊዜ (አስታውስ) ሰላም ያልታወቃችሁ ሕዝቦች ናችሁ አላቸው:: ከነርሱም መፍራትን በልቡ አሳደረ:: አትፍራ አሉት በአዋቂ ወጣት ልጅም አበሰሩት:: ሚስቱም እየጮኸች መጣች ፊቷን መታች መካን አሮጊት ነኝ አላችም እንደዚሁስ ጌታህ ብሏል እነሆ እርሱ ጥበበኛ አዋቂ ነውና አሏት:: አል ዛሪያት (51): 24፣25፣28-30*

ከዚህ በተጨማሪ ስለ አብረሃምና ይስሀቅ ጠቅላላ ሀሳብ የያዘውን ከቁርዓን እንደሚከተለው ተጠቅሶ እናያለን::

*ሰላም በኢብራሂም ላይ ይሁን እንደዚሁ መልካም ሰሪዎችን ሁሉ እንመነዳለን (እንሸልማለን) እርሱ በእርግጥ ካመኑት ባሮቻችን ነው በኢስሐቅም አበሰርነው ከመልካም የሆነ ነቢይ ሲሆን በርሱና በኢስሀቅ ላይም ባረክን:: ኢል ሷፋት (37):109-113*

«በአዋቂ ወጣት ልጅም አበሰሩት» የሚለውን እና «በኢስሐቅም አበሰርነው» የሚሉትን ሀረጎች በደንብ ይገነዘቧል:: እንደነዚህ ያለ ሀረግ ፈፅሞ በቁርአን ስለ ኢስማኤል አልተጠቀሰም:: ግልፅ ሲሆን የሚገባው ነገር የምስራች የተሰበረው እንደገናም ለመስዋዕትም ቀርቦ የነበረው ኢስማኤል ሳይሆን ይስሐቅ ነበር:: ሱራ 37:100-107 መፅሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚያስተምረውም ይህንኑ ነው::

በዚህ የውይይት ፅሁፍ ሙስሊሞች ልጅ የተባለው እስማኤል ነው ብለው እንደሚያምኑ ተገልጿል:: ሁሉም ግን አይደለም:: ቁርአንን በደንብ ያነበቡ ሙስሊሞች ነጥቦች ሁሉ የሚያመለክተው ኢስሀቅን እንደ ሆነ ይረዳሉ:: ለዚህም ነው የሱፍ አሊ በታወቀው የቁርዓን ማብራሪያ /commentary of holy qurian/ በገጽ 1204 ማስታወሻ ቁጥር 4096 እውነታውን እንደዚህ ያለው «ስለዚህ ወንድ ልጅ የተባለው እንደ ሙስሊሞች እምነት (በዚህ ላይ ይሁን እንጅ ሳይስማማ) የመጀመሪያው የአብርሃም ልጅ ኢስማኤል

ነው:: በዚህ ውስጥ የምናየው እንደ ሙስሊሞች እምነት እናም ይሁን እንጂ በዚህ ላይ የማይገጥም የሚሉትን ሀረጎች ማጤን አስፈላጊ ነው:: እናም የምንመለከተው ያ ልጅ የተባለው ኢስማኤል ነው የሚለው ከቁርዓን ፈፅሞ የማይገኝ ነው:: ቁርዓን የመጣው ያለፉትን ቅዱስ መፃህፍት ለማረጋገጥ ነው የሚለውን ሀሳብ ከተያዘ የሚቃረን ሀሳብ መፈጠር አይገባውም ነበር:: ስለዚህ በዚህ አንፃር ቁርዓን ከመጸሀፍ ቅዱስ የሚስማማ ቢሆንም የሙስሊም እምነት /አፈታሪክ/ ግን ከዚህ ጋር ይጋጫል::

## 6. ሙስሊሞች መጽሀፍ ቅዱስን ማንበብ አይገባቸውም

ብዙ ሙስሊሞችም መጽሀፍ ቅዱስ ማንበብ አስፈላጊ አይደለም ምክንያቱም ቁርአን የመጨረሻ የአላህ ቃል ነው መጽሀፍ ቅዱስንም ስለሚበልጥ ነው ይላሉ:: ይሁን እንጅ ቁርዓን ራሱ ሙስሊሞችን በሁሉም ቅዱሳት መጻህፍት እንዲያምኑ እና እንዲቀበሉ ነው:: የሚያዘው ቁርአን አይደለም:: ቁርአን አጥብቆ ሲያዝ እንዲህ ይላል: -

*በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማኤልና ወደ ኢስሀቅም ወደ ያዕቆብና ወደ ነገዶችም በተወረደው በዚያም በሙሳና ኢሳ በተሠጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱም በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን እኛም በርሱ (በአላህ) ታዛዦች ነን በሉ::*

*<u>ኢል በቀራህ (2): 136</u>*

*መልእክተኛው ከጌታው ወደርሱ በተወረደው አመነ ምእመኖችም (እንደዚሁ) ሁሉም በአላህ በመላእከቱም በመፃህፍቱም በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ በአንድም መካከል አንለይም (የሚሉ ሲሆኑ) አመኑ ሰማን ፣ ታዘዝንም ጌታችን ሆይ ምህረትህን (እንሻለን) መመለስም ወዳንተ ብቻ ነው አሉም::*

*<u>አል በቀረህ (2):285</u>*

እናንተ ያመናችሁ ሆይ በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መፅሀፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሀፍ እመኑ በአላህና በመላእክቱም በመጽሀፎቹም በመልእክተኞችም በመጨረሻውም ቀን የካደ ሰው የእውነት የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ::

«በመጽሀፎቹም» የሚለውን ቃል ልብ ይሏል:: ብዛትን ያሳያል ቁርዓንን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ቅዱሳት መጻሕፍትን ነው የሚያመለክተው:: ደግሞ የመጀመሪያ ጥቅስ ሀረግ «ከእነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን» የሚለውን መመልከት ተገቢ ነው:: ሙስሊሞች ማጤን ያለባቸው የቅዱሳን መጻህፍትን ማበላለጥ አይችሉም:: የእግዚአብሔር ቃል መመሪያዎች ለሁሉም ህዝቦች ለሁሉም ዘመን አይለያዩም:: አንድ

አይነት ናቸው። ለሙስሊሞችም ማስረዳት የሚገባው መጽሀፍ ቅዱስ አንድ ቅዱስ መጽሀፍ ብቻ አለመሆኑን ነገር ግን የብዙ ቅዱሳን መጻህፍት ስብስብ ሆኖ የሙሴን ሕግ ተውራትን የዳዊትን መዝሙር /ዘቡርን/ የኢየሱስ ትምህርቶች /ኢንጅልን/ እናም የነቢያትን ቃል (ሱራፍ ኢን ነቢይን) ማቀፍን ሊገባቸው ያስፈልጋል። ስለዚህ አንድ ሰው በእነዚህ መጻህፍት ሲያምን ማንበብ ብቻ ሳይሆን ማጥናትና የሚለውንም በትክክል ማወቅ ተገቢ ነው። ቁርዓንም በትእዛዙ እነዚያ መጽሀፍን የሰጠናቸው ተገቢ ንባቡን ያነቡታል እነዚያ በርሱ ያምናሉ በእርሱም የሚከዱ እነዚያ እነርሱ ከሳሪዎች ናቸው።

በእስላም ሌላው ተፈላጊ የሆነው ነገር ቅዱሳት መጻህፍት ከአላህ ዘንድ የሰውን ልጅ ለመርዳት የተሰጡ እንደሆኑ ይቆጠራሉ። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቀለም አያት (ምልክት) እንደሆነ ይታመናል። በተጨማሪም እነዚህ ምልክቶች ዝም ተብሎ ተወርተው የሚታለፉ ሳይሆኑ ሊቀበሏቸው የሚገባቸው ነገር ነው። የአላህን ምልክቶች ለሚንቁ ሁሉንም ቅዱሳት መጻህፍት ለማይቀበሉ ቁርዓን እንዲህ በማለት አደገኛ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

እነዚያን በተአምራታችን የካዱትን በእርግጥ እሳትን እናገባቸዋለን       አል-ኒሳእ/4/:56
እነዚያም የካዱና በተአምራቶቻችን ያስተባበሉ እነዚያ የእሳት ገጾች ናቸው።አል-ማኢዳህ /5/:10

## 7. መጽሐፍ ቅዱስ አስተማማኝ የመጀመሪያዎቹ ቅጂዎች ጠፍተዋል

ጥቂት ሙስሊሞች የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ስለጠፉ መፅሐፍ ቅዱስ አስተማማኝ አይደለም በማለት ይከራከራሉ። ስለዚህ የመፅሐፍ ቅዱስን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አንችልም ምክንያቱም የመጀመሪዎቹ ቅጂዎች ስለሌሉ ነው። በርግጥም አንድም የመጀመሪያ ቅጂ አልተገኘም ምናልባትም ጠፍተዋል ይሁን እንጂ ቁርአንም እንዲሁ ነው። የቅዱስ ቁርአን ማብራሪያና ትርጉም ፀሐፊ የሱፍ አሊ በመግቢያው ላይ ገፅ 32 እንዲህ ብሎ ያስቀምጣል: -

የቁርአን ንባብ የተገለጠው ወዲያውኑ ቅጠሎች በዛፍ ቅርፊቶች በአጥንቶች ወዘተ ተፅፈው ነበር። እናም እነዚህ ትንንሽ ጽሑፎች በከረጢት ውስጥ ተከማቹ።
ሁለተኛ እትም 1977 እ.አ.አ.

እንደዚህ ጽሑፍ የቁርዓን ጥቅሶች በቅጠሎች ፣ በዛፍ ቅርፊቶች በአጥንቶች ላይ ተፅፈው እንደነበሩ እንረዳለን። ከዚህ አለፍ ያለ ጥናት እንደሚያሳየው የቁርአን ጥቅሶች

በነጭ ድንጋዩች እና ወንዶች ደረት ላይ ተጽፈው እነደነበረ ሳላህ አል በኩሐሪ በተባለው መፅሐፍ ውስጥ ተዘግቧል:: ይህ ደግሞ የሱፍ አሊ ከመሠከረው ጋር አንድ ላይ አይሔድም:: በተጨማሪም አንድም ግለሰብም ሆነ ሙዚየም ምንም አይነት የቅጠል ፣ የዛፍ ቅርፊት ፣ ነጭ ድንጋይ ወይንም አጥንት ማስቀመጡን የገለፀ የለም:: ስለዚህ ሁሉም ቁርዓን ዛሬ ከጥንቱ ቅጂ በሙስሊሙ መሪ ኡትማን ከመሀመድ 20 ሙት አመት በኃላ መሆኑ ነው:: ሌላው ቅጂ በነብያቸው በመጀመሪያ የተሠጠውን ቅጂ ግን ማንም ሊያረጋግጥ አይችልም:: ሙስሊሙም ክርስቲያኑም ያለው ችግር አንድ አይነት ነው:: የመጀመሪያው ቅጂ ፈፅሞ አልተገኘም:: ሙስሊሙም ታዲያ ለቁርአናቸው ያላቸው ግምት ከመጀመሪያ ቅጂ ጋር ሳያወዳድሩም ከተቀበሉ ክርስቲያኞችም ለመጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው ግምት ሊቀበሉት ፣ ሊከብዳቸው አይገባም:: ለሙስሊም መጽሐፍ ቅዱስን መቀበል ሊያስጨንቀው አይገባም:: ቁርዓን ስለራሱ ሲናገር የቀደሙትን ቅዱስ መፅሀፍ ለማረጋገጥ እንደሆነ ይናገራል:: ይህ እውነት ከሆነ ሙስሊሙ የመጀመሪያው ቅጂ መሆን አለመሆኑ ምንም ሊያስቸግረው አይገባም:: መጽሐፍት ግልጽ የሆነ ስህተት ካለው ቁርአን ሊያረጋግጠው ሳይሆን የመጣው የሚባለው ለማስወገድ ለመተካት ወይንም ለማረም ነው ይባል ነበር:: ይሁን እንጂ ምንም አይነት ፍንጭ በቁርዓን አልተጠቀሰም:: ስለዚህ ሙስሊሙ በራሱ ቁርዓን ትዕዛዝ መሠረት በነፃነት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳትን መጻህፍት ሊቀበል ይገባዋል::

## 8. መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት አለበት ብዙ ቁጥሮች ይለያያሉ/ይጋጫሉ/

ጥቂት ሙስሊሞች አሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች ስለሚጋጩ በማለት ሊያሳጡት የሚጣጣሩት በፍጥነት የሚሉት መፅሐፍ ቅዱስ በእውነት የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ የቁጥር ስህተቶች አይታዮም ነበር:: ምክንያቱም እግዚአብሔር አይሳሳትም:: እርግጥ ነው እግዚአብሔር ፍፁም ትክክል ነው:: ይሁን እንጂ የሰው ልጆች ደግሞ ፍፁም አይደሉም:: ቃሉን የገለጠው እግዚአብሔር ቢሆንም የፃፉትና ቅጂዎችን ለሰዎች በየዘመናት የፃፉት የሰው እጆች ናቸው:: ህዝቦች ፍፁሞች ስላልሆኑ ብዙ ስህተቶች በሥራቸው ውስጥ ሲገኝ ይችላል:: ይህንን ስህተት የቅጂዎች ስህተት ነው የምንለው ይህም ደግሞ አስቸጋሪና ከባድ ሥራ በነበረበትና የማባዣ መሳሪያዎች በሌሉበት ዘመን ስለ ነበረ ነው:: ይህም ከኬጂቪ (K.J.V) የተወሰደ እንደምሳሌ ልናየው እንችላለን::

*ዳዊትም ከእርሱ ጋር አንድ ሺ ሰረገላዎች ሰባት መቶ ፈረሰኞች እና ሃያ ሺ እግረኛ ሰራዊት ይዞ ወሰደ:: 2ሳሙ 8:8*

*ዳዊትም ከእርሱ ጋር አንድ ሺ ሰረገላዎች ሰባት ሺህ ፈረሰኞች እና ሃያ ሺህ እግረኛ ሰዎች ወሰደ:: 1ዜና 18:4*

እንደምንመለከተው የመጀመሪያው ስለ 700 ፈረሰኞች የሚቀጥለው ግን 7000 ፈረሰኞች እንደሆነ ይናገራል:: ብዙ እንዲህ ያሉ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ሊኖሩ ይችላሉ:: እና ምክንያቱም ብዙዎቹ የዕብራውያን ቁጥሮች ባሕርይ አንዱ ከሌላው ስለሚቀራረቡ ነው:: ስለዚህ አንዱን ቁጥር ወደሌላ የመለወጡ አጋጣሚ በቅጂዎቹ ስህተት ሊፈጠር የሚችል ነው:: በሌላም አጋጣሚ ዜሮ ቁጥርን የመቀነስ አጋጣሚ 7000 የነበረውን 700 እንደሆነ ተቀድቶ ይሆናል:: እንዲህ ያሉ ስህተቶች በመጀመሪያው ቃል ላይ እንደማይኖር ይታመናል:: የሚገባው ነገር ቢኖር እንዲህ ያሉ ስህተቶች የእግዚአብሔርን ቃል ሙስሊሙ ሊያውቅ መሰረታዊውን አስተምህሮ ሊለውጥ አይችልም ለምሳሌ: ተመሳሳይ ችግር በቁርዓንም ውስጥ አለ::

*ከዚያም ከምትቆጥሩት (ዘመን) ልኩ ሺ ዓመት በሆነ ቀን ውስጥ ወደርሱ (አላህ) ይወጣል (ይመለሳል) መላእክቱና መንፈሱም ልክ አምሳ ሺ አመት በሆነቀን ውስጥ ወደርሱ ያርጋሉ::* *አል መአሪጅ (70):4*

በእነዚህ ክፍሎች ስንመለከት አንዱ ቀን ከአላህ ጋር እንደ 1000 አመታት ሲሆን በሌላው ክፍል አንዱ ቀን ወደ 50000 አመታት ጋር እኩል እንደሆነ ያመለክታል:: ቢሆንም ይህ የቁጥር መለያየት በምንም መንገድ ቁራዓን ከሚያስተምረው ከአላህ ሩህሩህነት ፣ መሀሪነት ፣ ሁሌም ሀጢያት ይቅር ከሚለው ትምህርት ጋር አይጋጭም:: በተመሳሳይ ሁኔታ በ6300 ፈረሰኞች ቁጥር ልዩነት መጽሀፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ የሆነው በመሲሁ ኢየሱስ የተገለጠውን ምህረት እና ርህራሔ የሚያፈናቅል አይደለም:: በመሲሁ ኢየሱስ በኩል መዋጀትና የሀጢያት ይቅርታም ይገኛል::

## 9. መሀመድ አዲስ ሀይማኖት ለመመስረት ነው

በጥቂት የሙስሊም እምነት ተከታዮች ዘንድ እንደ የሚገባው መሀመድ የመጡት አዲስ ሀይማኖትን ፣ አዲስ ህግን በመስጠት የተሳሳተውን እኛን ዘመን ያለፈበትን የአይሁዶችን ሃይማኖት በመመስረትና የክርስቲያኖችን ሀይማኖት ለመተካት ነው:: በዚህ ምክንያት ብዙ ሙስሊሞች ለክርስትና መልዕክት ጆሮአቸውን አይሰጡም:: እንደነሱ የክርስትያን ሀይማኖት በአዲሱና በሚሻለው የእስላም እምነት የተበለጠ ነው እናም አዲሱ የእስልምና ሀይማኖት ከኢየሱስ ዘመን ወዲህ ከ600 ዓመታት በኃላ በመሀመድ አማካኝነት ተመስርቷል ይላሉ:: ይሁን እንጂ እንዲህ አይነቱ ትምህርትም ሆነ አስተሳሰብ ከቁርአን

አስተምህሮ ጋር የማይሄድ ነው:: በቁርአን መሰረት የመሀመድ ተልእኮ አዲስ ሀይማኖት ለመመስረት ሳይሆን የአብርሃምን ሀይማኖት መቀጠል ነበር::

*ከዚያም ወደ አንተ የኢብራሂምን ሃይማኖት ቀጥተኛ ሲሆን ተከተል ከአጋራዎቹም አልነበረም ማለትን አወረድን::* *አል ነሕል (16)123*

*እኔ ጌታዬ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትክክለኛን ሃይማኖት ወደ እውነት አዘንባይ ሲሆን የአብርሃምን መንገድ መራኝ እርሱም ከአጋሪዎቹ አልነበር ሲል:: አል - አንዓ (6)161*

*አላህ እውነትን ተናገረ የኢብራሂምንም መንገድ ወደ እውነት ያዘነበለ ሲሆን ተከተሉ ከአጋሪዎቹም አልነበረም በላቸው::* *ኢ.ሊ ዒምራ (3)95*

አይሁድ ወይም ክርስቲያን ሁኑ (ቅኑን መንገድ)ትመራላችሁና እሱም አይደለም የኢብራሂምን ሃይማኖት ቀጥተኛ መንገድ ሲሆን እንከተላለን:: አል በቀራህ

*እርሱ መልካም ሰሪ ሆኖ ፊቱን ለአላህ ከሠጠና የኢብራሂም መንገድ ቀጥተኛ ሲሆን ከተከተለ ሰው ይበልጥ ሃይማኖቱ ያማረ ማነው? አላህ ኢብራሂምን ፍፁም ወዳጅ አድረጎ ያዘው:: አል - ሂሳን (9)125*

ከላይ ከጠቀስነው ተጨማሪ ቁርአን ራሱ የሚናገረው መሀመድ አንዳች አዲስ ነገር በማስተመር አልመጣም በእርግጥ ቁርዓን እንደሚነግረን መሀመድ የተሠጠው ያለፈውን ማረጋገጫ አዲስ ነገር እንዳለው አይደለም::

*ከበፊቱም የሙሳ መጽሐፋ መሪና ፀጋ ሲሆን አልለይህም እነዚያን የበደሉትን ሊያስፈራራ በዓረብኛ ቋንቋ ሲሆን (የፊቶቹን) አረጋጋጭ መጽሐፋ ነው ለበጎ አድራጊዎችም ብስራት ነው::* *አል-አሕቃፋ (46):12*

*ከአንተ በፊት ለነበሩት መልዕክተኞች የተባለው ብጤ እንጂ ለአንተ ሌላ አይባል ጌታህ የምህረት ባለቤትና የአሣማሚ ቅጣት ባለቤት ነው::* *አል-ሶጅዳህ (41)43*

*ለናንተ ከሃይማኖት ያንን በርሱ ኑሕን ያዘዝንበትን ደነገገላችሁ ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን ያንንም በርሱ ኢብራሂምን ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን ሃይማኖትን በትክክል አቀቁሙ በእርሱም አትለያዩ ማለትን (ደነገግን)::* *አል-ሹራ(42)13*

*ከመልክተኞች ብጤ የሌለኝ አይደለሁም በኔም በእናንተም ምን እንደሚሠራም አላውቅም ወደኔ የሚወረደውን እንጅ ሌላን አልከተልም እኔም ግልጽ አስፈራሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው:: አል-አሕቃፉ (46)9*

የአብራሂም ሐይማኖት የሰፋው የሥነ-ምግባርና ማህበራዊ ሕጎች እግዜአብሔርን ሲከተሉ ለነበሩት በነብዩ ሙሴ አማካኝነት በመሥጠቱ እንደሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነው:: ስለዚህ የእስላም ሀይማኖት ሥርዓቱ የተመሠረተው የታወቀና አዲስ ባልሆነ ልምድ ላይ በተለይ አይሁዶች መሀመድ ሳይመጡ በመቶዎች አመታት ቀድሞ ይኖሩበት የነበረ ነው:: ሙስሊሞች ስለክርስቲያኖች ካላቸው አመለካከት በተቃራኒ አዲሱ የተባለው የእስላም ሀይማኖት የሚከተለው ወግ ከመጽሐፉ ቅዱስ ተጓዳኝነት ያለው ነው::

1. ሰላምታ ሰላም (ሉቃ 10:5)
2. ከስግደት በፊት መታጠብ (ዘፀ 40:31 32)
3. በእግዚአብሔር ፊት ሲቀርቡ ጫማ ማውለቅ (ዘፀ 3:5)
4. በስግደት መፀለይ (መዝ 95:6)
5. የእንስሣት መስዋዕት(ዘዳ: 16 1-16)
6. መሳለም (ቅዱስ ቦታ) (ሐዋ.ሥ 8:26 - 28)
7. የሴቶች ራስ መሸፈን ( 1ቆሮ.11:5 6)
8. መገረዝ (ሉቃ 2:21)
9. ልጅ ሲወለድ መስዋዕት ማቅረብ (ሉቃ 2:24)
10. የረጅም ጊዜ ፀሎት (ዘፅ 34:28፣1ነገ 19:8፣ ማቴ 4:2)
11. የሴቶተ ጭምትነት ዝምተኛነት (1ቆሮ 14:34)
12. አሣማ ሥጋ ከመብላት መታቀብ (ዘሌ 11:7)

## 10. ኢየሱስ ለእሥራኤል ብቻ ነብይ ነበር

አንዳንድ ሙስሊሞች የኢየሱስ አገልግሎት ለእስራኤል ልጆች ብቻ እንጂ ለሁሉም ሕዝብ አይደለም ክርስቲያኖች እንደሚያስቡት ብለው ይከራከራሉ:: በዚህ ክርክር መሠረት ክርስቲያኖችን ለማሳመንና የመሀመድ ተከታዮች እንደሆኑ በመጎትጎት የመሀመድ የሁሉ ህዝቦች አቀፍ ነቢይነት በግልፅ ያውጃሉ:: ይህንኑ ሀሳባቸውን ለማጠናከር እነዚህ ሙስሊሞች የሚከተሉትን የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች በፍጥነት ያሳያሉ::

*እንዲሁም አለ: - በአህዛብ መንገድ አትሒዱ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ ይልቅስ የእራኤል ቤት ወደሚሆኑ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ እንጂ:: ማቴ 10:5-6*

*እርሱም መልሶ ከእሥራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ::*

*ማቴ 15:24*

ከሁሉም አስቀድመን ልንመለከት የሚገባን ኢየሱስ የተወለደው ከኢብራሂም ይስሀቅ እና ያዕቆብ ዘር መሆኑን ነው:: ከብዙ ክፍለ ዘመን በፊት ለአብርሃም የተገባው የተስፋ ፍፃሜ ኢየሱስ ነበር:: የአብርሃም ለእግዚአብሔር መገዛትና መታዘዝ እግዚአብሔር እጥፍ ተስፋ እንደሠጠው አደረገ:: በመጀመሪያ እግዚአብሔር ዘሩን ሁሉ እንደሚባርክ ሁለተኛ ከአብርሃም ዘር ለሕዝቦች ሁሉ በረከት የሚሆን እንደሚያስነሳ ነበር::

በዚህ ለአብርሃም በተገባው ተስፋ መሠረት ሁለቱም የእስራኤል ዘር እና አህዛብ የበረከቱ ባለቤት እንደሆኑ ነው:: ይህ ደግሞ ኢየሱስ ሲወለድ ተረጋገጠ:: ሕፃኑ ኢየሱስ ሲወለድ ለመንፃት ስርዓት ወደ ቤተመቅደስ ሲወሰድ አንድ ትጉ በእድሜ የገፋ ሽማግሌ በመንፈስ ቅዱስ ተነድቶ ሕጻኑን በክንዶቹ ታቀፈና በፀሎት ሲናገር እንዲህ አለ::

*አይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋል እና ይኸም ለአሕዛብ ሁሉ የሚገልጥ ብርሃን ለህዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው::* <u>*ሉቃ 2:30-32*</u>

ከላይ በተጠቀሰው መሠረት የምንረዳው የኢየሱስ አገልግሎት ድርብ አገልግሎት ነበር:: በመጀመሪያ ከእሥራኤል ልጆች ዘር ስለነበር ቀዳሚ ተልዕኮው ራሱን እና እግዚአብሔር ለእሥራኤል ልጆች መግለፅ ነበር:: እነሱ በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች ናቸው:: የአብርሃም የይስሀቅ እና የያዕቆብ ልጆች ናቸው:: ቁረዓንም እራሱ ይህንኑ ይመሠክራል:: እንዲህ ሲል: -

*ባሮቻችንንም ኢብራሂምን፣ ይስሀቅንና፣ ያዕቆብንም የሀይልና የማስተዋል ባለቤቶች የሆኑትን አወሳላቸው (አስባቸው) እኛ ጥሩ በሆነች ጠባይ መረጥናቸው እርሷም የመጨረሻይቱን ሀገር ማስታወስ ናት:: ሷድ (38)45-46*

*የእስራኤል ልጆች ሆይ ያችን በእናንተ ላይ የለገስኳትን ፀጋዬን እና እኔም በዓላማት ላይ ያበለጥካችሁ መሆኔን አስታውሱ::* <u>*አል - በቀራህ (2)47*</u>

የሚያሳዝነው ነገር በዘመናት ሁሉ የእስራኤል ልጆች ልበ-ጥጥሮችና ለእግዜአብሔር ግዴለሽ መሆናቸው ነው:: በዚህ ምክንያት ኢየሱስ በአካል በመሀከላቸው በመሆን በምልክትና በተዓምራት ለዘመናት ሲጠበቅ የነበረው መሲህ መሆኑን አረጋገጠላቸው:: የተባረከውና የተቀባው በእግዚአብሔርም የተላከው እስራኤልን ለመቤዠት ነበር ፣ እናም በሥጋ ወራቱ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ወደ እስራኤል ልጆች ብቻ እንዲሔዱ አዘዛቸው:: በቅድሚያ ወንጌል ሊሠሙ የሚገባቸው እነርሱ ነበሩ ጌታ የሠጣቸው እድል ምክንያቱ የኪዳኑ ሕዝቦች በመሆናቸው ነበር ያም ኪዳን የበረከት ኪዳን ነበር:: የሞቱን እና ትንሳኤውን ተከትሎ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ ሲናገር እንዲህ አለ::

*እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ከአባቶቻችን ጋር ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ:: ለእናንተ አስቀድሞ እግዜአብሐር ብላቴናውን አስነሥቶ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ ሰደደው:: ሐዋ.ሥ 3:25-26*

*ማረጋገጥ የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር ሁለተኛው የኢየሱስ ተልዕኮ ከሁሉም የላቀ ነበር:: ያተልዕኮ የራሱን ህይወት ለሰዎች ሁሉ ሀጢያት በመስጠት እነርሱን ማዳን ነው:: (1ጢሞ2:4-6)*

ይህ በረከት ነው ለሕዝቦች ሁሉ የመጣው ደሙን በመስቀል ላይ በማፍሰስ የሰውን ዘር የሀጢያት ቅጣት ከፈለ:: ማንም ይህንን የደህንነት በረከት ቢቀበል ለዘላለም ህይወት አስተማማኝ ዋስትና ያገኛል::

*እንዲሁም አላቸው ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሳል በስሙም ንስሀና የሀጢያት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተፅፏል:: ሉቃ 24:46-47*

የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ደህንነት በመሲሁ ኢየሱስ አማኝነት ለሰዎች ሁሉ ለአይሁድም ለአህዛብም እንደሆነ ያስረዳል:: አስታውሱ ኢየሱስ በምድር አገልግሎት ላይ አገልግሎቱ ደቀመዛሙርትን ያዘዛቸው ወደ እሥራኤላውያን ብቻ እንዲሔዱ ነበር:: ነገር ግን ሁለተኛውን ተልዕኮ ካከናወነ በኋላ (በመስቀል ሞት የሀጢያት ስርየት) እነዚያኑ ደቀመዛሙርት እንዴት ብሎ እንዳዘዛቸው ልብ በል::

*በኢየሩሳሌምም፣ በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከምድር ዳር ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ:: ሐዋ ሥ 1:8*

*እንግዲህ ሂዱና አህዛብ ሁሉ . . . ደቀመዛሙርት አድርጓቸው:: ማቴ 28:19*
ኢየሱስ ራሱ ተልዕኮው ሁሉን አቀፍ መሆኑን ሲያረጋግጥ እንዲህ አለ

*እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የህይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም:: ዩሐ 8:12*

ደግሞም ኢየሱስ ራሱ ለሰዎች ሁሉ ልዩ በረከት ወይም ልዩ ምህረት እንደሆነ ገልጿል:: ቁርዓንም የሚያመለክተው የኢየሱስ ተልዕኮ ሁሉን አቀፍ እንደሆነ ነው እግዜአብሔር የተናገረውን ቁርዓን ሲናገር: -

*ለሠዎችም ታምር (አያት አል-ሊናስ) ከኛም ችሮታ ልናደርገው (ይኸንን ሠራን) የተፈረደም ነገር ነው:: መርየም (19)21*

እንደምናስተውለው «ለእስራኤል ብቻ የተሰጠ ምልክት» አይደለም የሚለው:: በእውነቱ ከሆነ የአረብኛው ቅጂ «ለሰው ልጆች ምልክት» ነው የሚለው::

## 11. ኢየሱስ ከነቢዩ የሚበልጥ አልነበረም

የኢየሱስን ልዩ መሆን ለመሰወር በሚያደረጉት ጥረት ሙስሊሞች የሚከተለውን ይጠቅሳሉ::

*የመርያም ልጅ አልመሲህ ከበፊቱ መልእክተኞች በእርግጥ ይለፍ የሆነ መልክተኞች በእርግጥ ያለፈ የሆነ መልክተኛ በእርግጥ ያለፈ የሆነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም:: አል-ማአዳህ (5)75*

እርግጥ ነው ኢየሱስ በሰብአዊነቱ የታወቀ ነው:: ሥጋ የለበሰ ሰው ልክ እንደሌሎቹ ነቢያት ሰው ነበር:: ይሁን እንጂ ቅዱስ መፅሐፍ ቃል የሚገልጠውን እውነት ስናይ ግን በዚህ ስጋ በለበሰ ሠው ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍት የመለኮትን ባሕርይ የያዘው የእግዜአብሔር ቃል በውስጡ አድሯል:: ዮሐ 1:14 «ቃልም ስጋ ሆነ በእኛ መካከል አደረ» ይላል:: ይኸንን እውነት ገልጠን ማስረዳት ባንጀምርም ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ኢየሱስ መለኮታዊና ሰብአዊ ሰውነትና መለኮትነት ቁርዓን የሚያሳየው እውነት ነው::

*እናንተ የመጽሐፍ ሰዎች ሆይ (አይሁድና ክርስቲያኖች) በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ በአላህም ላይ እውነት እንጂ ውሸት አትናገሩ የመርየም ልጅ አልመሲህ ዒሳ የአላህ መልዕክተኛ ወደ መርየም የጣለት (የሆነ) ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስ ብቻ ነው:: አል ኒሳእ (4) 171*

ቁርአን በጊዜው ለነበረው የስህተት ትምህርት የመከላከል እና ኢየሱስ ከሦስቱ አማልክት አንዱ ነው ለሚለው ትምህርት የማስተካከያ ቃል የያዘ ሲሆን ቁርአን የኢየሱስን ልዩ መሆን በመለኮታዊ ክብር መኖሩን «የእርሱ/አላህ/ቃል» እና ከእርሱ /ከአላህ/ የሆነ መንፈስ በማለት ይገልፀዋል::

አዲስ ኪዳንም ኢየሱስን «የእግዚአብሐር ቃል» ይለዋል:1 (ራዕይ 19:13) ይህም ቃል በቀላሉ ሊታይ አይገባውም:: ብዙዎቹ ሙስሊሞችም ያለምንም ማንገራገር የእግዚአብሐር ቃል የሚፈጠር፣ የሚሞት እንዳልሆነ ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖር እንደሆነ ይቀበሉታል:: እንዲህ ያለው መለኮታዊነትን ያመለክታል::

«ከእርሱ የሆነ መንፈስ» የሚለው ሀረግ በአረብኛው ሩሀ ዑን ሚንሁ ሲሆን በቁርዓን ውስጥ በየትኛውም ክፍል ይገኛል:1

*በልቦቻቸው ውስጥ እምነት ጽፏል ከርሱም በሆነ መንፈስ ደግፏቸዋል::*
*አል-ሙጃደላህ (58):22*

በቅዱስ ቁርዓን ትርጉም እና ዝርዝር ሀተታው ላይ የሱፍ አሊ ይኸንን ሲገልፅ «ከራሱ የሆነ መንፈስ» የሚለውን ሀርግ» ትርጉሙን በሰብአዊ ቋንቋ ለመግለፅ ከመሞከር ቢቀር በትክክል መነገር የማይቻል የእግዚአብሔር ባህሪና ተፈጥሮ የሆነ መለኮታዊ መንፈስ» ይለዋል:: የግርጌ ማስታወሻ 5365

ከላይ እንዳየነው የአረብኛው ሀረገ ሩኸዑን ሚንኹ የሚለው ኢየሱስን መግለፁ ነው:: አል-ኒሳእ (4):171 የሚለውም ከነብይ በላይ ስለሆነው ኢየሱስ ነው::

ስለኢየሱስ ልዩ መሆን በቁርዓን ማንኛውም የተዘረዘሩትን ልብ ይሏል::

## ሀ. በተዓምር ከድንግል መወለዱ

*እርሷም (መርየም) በጋብቻ ሠው ያልነካኝ ሆኜ አመንዝራም ሳልሆን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል አለች::* *መርየም (19):20-21*

አንዳንድ ጊዜ አዳምም የተፈጥሮ አባት እንደሌለው ይገለጣል:: ስለዚህ ኢየሱስም ልዩ እንደሆነ ተደርጎ ሊታይ አይገባም:: እርግጥ ነው:: አዳም ምድራዊ አባት አልነበረም ሆኖም ሊኖር ያስፈልግ ነበር:: እንዴት የተፈጥሮ አባትና እናት ሊኖር ይችላል አዳም መጀመሪያ ሠው እስከሆነ ድረስ? ይሁን እንጅ ይህ ከኢየሱስ ፍፁም የተለየ ነበር:: በሙቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች ኢየሱስም ከእርሱ ሊወለድ እንደሚችል ልክ ከአዳም በኋላ እንደተወለዱት ነቢያት ሊወለድ ይችል ነበር:: ሆኖም ይህ እግዚአብሔር የተጠቀመበት ምልክት ሲሆን ለእርሱ የተፈጥሮ አባት ሳይኖር ራሱ ከእግዚአብሐር መለኮት ባህርይ የመጣ ሆነ::

## ለ. ቅዱስ ህይወት ኖረ

*እኔ ንጹሕን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ የጌታሽ መልክተኛ ነኝ አላት::* *መርየም (19):19*

ኢየሱስ በእርግጥ ቅዱስ ልጅ ነበር:: ከእግዚአብሐር ዘንድ የመጣ እንጂ ከወንድ ዘር ስላልነበር ሰይጣን በወሊድ ላይ ሠይጣን አልዳሠሠውም:: በእውነት ኢየሱስ ንፁህ ሕይወት ኖረ ነቀፋም አንድ እንኳ አልነበረበትም:: ብዙ ሙስሊሞች ሁሉም ነቢያት ነቀፋ እንደሌላቸው ስለሚገምቱ የኢየሱስ ልዩ መሆን አይታያቸውም:: ይሁን እንጂ ቁርዓን

የሚለው እንዲህ አይደለም። ታላለቅ ነቢያት የተባሉት እንኳን ስለሀጢያታቸው ምህረትን ለምነዋል። ኢየሱስ በተወለደበት መንገድ ሳይሆን እንደ ሌሎች ወንዶች ሁሉ ነቢያትም ከአዳም ዘር ነው የተወለዱት። የሚከተሉትን ልብ ይሏል።

*አዳም - ጌታችን ወደ (አዳምና ሔዋን) ነፍሶቻችንን በደልን ለኛ ባትምር ባታዝንልንም በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንሆናለን አሉ።*

*አል-አዕራፍ (7)23*

*አብርሃም - ያም በፍርዱ ቀን ኃጢአቴን ለኔ ሲምር የምከጅለው ነው።*

*አል-ሽዐራ (26):82*

*ሙሴ - ጌታዬ ሆይ እኔ ነፍሴን በደልኩ ለኔም ማር አለ ለርሱም ምሕረት አደረገለት እርሱ መሃሪ አዛኝ ነውና።* *አል-ቀሰስ (28):16*

*ዳዊት - ዳውድም የፈተንነው መሆኑን አወቀ ጌታውንም ምህረትን ለመነ።*

*ሷድ (38):24*

*ሰለሞን - ጌታዬ ለኔ ማር .. ።* *ሷድ (38):35*

*ዮናስ - እርሱም ተወቃሽ ሲሆን ዓሳው ዋጠው እርሱ ለጌታው አወዳሾቹ ባልሆነም ኖሮ እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድርስ በሆዱ ውስጥ በቆየ ነበር።*

*አል-ሷፍፋት (37):142-144*

*መሐመድ - እኛ አንተ (መሀመድ) ግልጽ የሆነን መክፈት አፋትንልህ አላህ ከሀጢያትህ ያለፈውንና የሚመጣውን ላንተ ሲምር ጸጋውንም ባንተ ላይ ሲሞላ ቀጥተኛ ውንም መንገድ ሊመራህ (ከፈተልህ) ።* *አል-ፈትሕ (48):1-2*

*እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩን ዕወቅ ስለ ስህተትህም ለምዕመናን ምህረት ለምን አላህም መዘዋወሪያችሁን መርጊያችሁንም ያውቃል።* *መሀመድ (47):19*

አንድ ሠው ቁርዓን በደንብ የሚለውን ቢያጠና አንድም ጥቅስ ኢየሱስ ምህረት ሲለምን አንመለከትም። ምክንያቱም ግልፅ መሆን አለበት። ቅዱስ፣ነቀፋ የሌለበት ፍፁም ንፁህ ስለነበር ነው። እርሱ ከላይ የመጣ እንጅ ከዚህ አለም አልነበረም።

## ሐ. ታላላቅ ተአምራትን አከናወነ

*እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣችሁ:: እኔ ለእናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ በርሱም እተነፍስበታለሁ በአላህም ፈቃድ ዕውር ሆኖ የተወለደን ለምጻሞንም አድናለሁ ሙታንንም አስነሳለሁ ... አል-ኢምራን (3):49*

ኢየሱስ ያደረገው ታላላቅ ተዓምራቶች የሞቱትን ማስነሳት እና የታመሙትን መፈወስ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ከእርሱ በፊትና ከእርሱ በኋላ ያላደረጉትን ቁርዓን እንደሚያስተምረው በርግቧ ቅርፅ በማውጣተ በውስጧም ትንፋሹን በማስገባት ህያው ፍጡር ሆና እንድትኖር አደረገ::

## መ. የእግዚአብሔር ሕልውና ወዳለበት ተመለሰ

*ዒሳ ሆይ እኔ ወላጅህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ:: አሊ-ዓምራን (3):55*

እንደ ሌሎች ነቢያት ኢየሱስ ወደ አፈር ገብቶ አልቀረም የተወሰደውም ወደሰማይ ብቻ ሳይሆን የተወሰደው ከዚህ ለየት ባለ ሆኔታ ወደ እግዚአብሐር ወደ ራሱ ነበር:: ቅዱሳት ጽሑፎች የሚናገሩት ሌሎች ነቢያት እንዲህ ያለ ክብር አላገኙም:: ኢየሱስ ከላይ ስለነበር ከራሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለነበር በቁርዓን መሠረት በትክክል ኢየሱስ ተመልሶ የሔደበት መገለፁን ልብ ይሏል::

## ሠ. ወደእዚህ አለም ተመልሶ ይመጣል

*እርሱም (ዒሳ) ለሰዓቲቱ (ማወቂያ) በእርግጥ ምልክት ነው (ፍርድን ሠዓት):: አል-ዙክሩፍ (43):61*

ኢየሱስ ዳግም ከሠማይ እንደሚመጣ ቁርዓን በግልጽ ባያስተምርም ብዙ ሙስሊሞች ፀሐፊዎች የሙስሊሙን ስለኢየሱሰ በመጨረሻውም ቀን ሰይጣንን ድል ለመንሳት እና ሁሉን አቀፍ ሠላም ለመምጣት ፣ ለማመቻቸት እንደሚመለስ ያለውን እምነት ለመደገፍ ከላይ የተጠቀሠውን ይጠቀማሉ:: ቅዱስ ቁርዓን በሚለው ትርጉምና ማብራሪያ መፅሐፍ የሱፍ አሊ ከላይ የተጠቀሠውን ክፍል ሲያብራራ «ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው የኢየሱስን ዳግም ምጽዓት ያሳያል ይህም ከትንሳኤ በጥቂት ይቀድማል»

ለመከለስ ያህል ከላይ በቁርዓን የተዘረዘሩት ጥቅሶች በሙሉ ኢየሱስን የሚስሉት ከአዳም ደም ምንጭ ውጪ በሆነ ተአምራዊ መንገድ እንደተወለደ፣ ሐጢያት የማይሠራ እንደሆነ ታላላቅ ተአምራት እንዳከናወኑ፣ ፈጣሪ እንደሆነ፣ወደ ራሱ ወደ እግዚአብሐር እንደተወሰደ እናም ወደዚህ አለም በመምጣት ለሁሉም የሰላምን መንገድ እንደሚከፍት

ነው:: ሌላ ነብይ በምንም ዓይነት መንገድ እንደዚህ የሚሆን እንደሌለ ቅድሳት መፃህፍት ይመሰክራሉ አንዳንድ ሙስሊሞች እንደሚሉት ሳይሆን ቅዱስ ቁርዓን ድምጹን ከፍ አድርጎ የሚናገረው ይሕ ከማንኛውም ነቢይ የተለየ እንደሆነ ነው::

## 12. ክርስቲያኖች ሦስቱን አምላኮችን ያመልካሉ

* እጅግ ከተለመዱት እና ጠንካራ ከሆኑ ተቃውሞዎች አንዱ ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን ሶስት አማልክት ያመልካሉ የሚል ነው:: «ስላሴ» የሚለው ቃል ለሙስሊሞች እጅግ የተሳሳተ አስተሳሰብ ስለሚያመጣ ክርስቲያኖች የሚያመልኩት አንድ ብቻ ሳይሆን ሦስቱ አማልክት ናቸው የሚል ነው:: ይኸ ደግሞ እስልምና ተከታይ ሊሆኑት ከልጅነታቸው ጀምሮ እጅግ የከፋ ሀጢያት ማድረግ ነው::

— እጅግ የሚያሳዝነው መሀመድ በነበሩበት ዘመን በስህተት ውስጥ የወደቁ ጥቂት ክርስቲያኖች በአርብ ምድር ነበር:: እነርሱም ማርያም ልክ እንደ እየሱስ አምላክ ነች ብለው ይናገሩ ነበር:: እነርሱም እግዚአብሔር አባት ፣ ማርያም ልክ አንደ ኢየሱስ እናት ፣ እየሱስ ልጅ ሦስቱም አምላኮች እንደሚያመልኩ አድረገው ያስተምሩ ነበር:: በእርግጥ ይህ አይነቱ አስተምህሮ ፈፅሞ መፀሐፍ ቅዱስን የሚጋጭ ነገር ነው:: ይህንን ቁርዓን የሚቃወመው::

- *የመርያም ልጅ ዒሳ ሆይ አንተ ለሰዎቹ እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን? አል-ማኢዳህ (5) :116*

*እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው ያሉ በእረግጥ ከዱ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጅ ሌላ የለም:: አል-ማኢዳህ (5) :73*

- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥላሴዎችን አስተምህሮ በተሳሰተ መንገድ ስለተረዱት ስለዚህም ሙሰሊሞች አጥብቀው ስለሚቃወሙ «ስላሴ» የሚለውን ቃል በማስተማር ጊዜ ልናባክን አይገባም:: ለሙስሊሙ ጓደኛችን እኛም የምናመልከው አምላክ አንድ ነው ብለን ማስረዳት እንጂ ስላሴ የሚለውን ቃል አለመጠቀሙ ይመረጣል:: መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ስለ እግዚኢብሔር አንድነት ዘዳ 4:35 ዘዳ 6:4 እና ማርቆስ 12:29 ላይ ያለውን ተጠቀም:: ይሁን እንጂ አንድ አምላክ እንዳለ የራሱ ፈቃድም እንዳለው ይህንን ፈቃዱን በቃሉ እንደሚገለጥ እናም በመንፈሱ እንደሚያከናውን፣ መንፈሱ እና ቃሉ ባሉበት እግዚአብሔር እንዳለና እደሚመለክ ሙስሊሙ ይወቅ:: ይህ እውነታ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የሚዘረዝረውን እግዚአብሐር ቃልን እንደተናገረ በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ፍጥረት ሁሉ ህያው እንደሆነ የተገለጠ ነገር ነው:: (ዘፍ 1:1-3 መዝ 33:6 ,104:24) ለጓደኛህ ሁለቱም

የእግዚአብሐር ቃልና የእግዚአብሐር መንፈስ ከእግዚአብሐር ሊነጠሉ የማይችሉ እንደሆኑ ግለፅለት። እግዚአብሔር እስካለ ድረስ ቃሉም ሆነ መንፈሱ ይኖራሉ የተፈጠሩ አይደሉም አይሞቱም እናም መለኮት ናቸው።

አስደናቂው ነገር ለብዙ ሙስሊሞች ያልታወቀ ቁርዓን ግን ሦስት ነገሮች መለኮት መሆናቸውን ያሳያል። እርግጥ ነው የመጀመሪያው እራሱ እግዚአብሔር ነው ነገር ግን ደግሞ ቁርዓን ደግሞ ስለእግዚአብሐር ቃል ይነገራል ይህም ቃል ወይንም የፍጥረተ ሁሉ ትዕዛዝ ይባላል።

*ለማንኛውም ነገር (መሆኑን) ባሻነው ጊዜ ቃላችን ለእርሱ ሁን ማለት ብቻ ነው ወዲያውም ይሆናል።   አል-ነሕል(16):40*

*ነገሩም አንዳችን በሻን ጊዜ ሁን ማለት ነው ወዲያው ይሆናልም። ያሲን (36)82*

ከላይ ባየነው በ36:82 መሠረት በቅዱስ ቁርዓን ትርጉምና ፍቺው የሱፍ አሊ እንደዘረዘረው «እግዚአብሔር በፈለገበት ቅጽበት አንድ ነገር ይፈቅዳል እናም ቃሉ ወይም ትዕዛዝ ይሆናል። ይህም ሕያው ሆኖ ይታያል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያዎች ደግሞ ፍጥረታት ሁሉ በእርሱ እንደተፈጠሩ ሲናገር ፈጣሪ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ተፈጣሪ አለመሆኑን ያረጋግጣል። እርሱ ፍጥረታት ሁሉ ወደ ህያውነት የመጡበት ወኪል ነው። በዚህ ብዙ ሙስሞች የሚስማሙበት እንዲሆን ሲገልፁ «ልክ ነው የእግዚአብሔር ቃል አይፈጠርም» ይላሉ። እናም የእግዚአብሔር ቃል የማይፈጠር እና ዘላለማዊ ከሆነ ያለምንም ጥርጥር እርሱ መለኮት ነው። በዚህ ዝርዝር እውነታ ተመስርተን ለሙስሊሙ ጓደኞችን የምንለው ኢየሱስ ሰው ብቻ ሳይሆን መለኮት መሆኑንም ጭምር ነው። ቁርዓንም መጽሐፍ ቅዱስም «የእግዚአብሔር ቃል» ብለው ያረጋግጣሉና።

ሦስተኛው ነገር ቁርዓን የእግዚአብሔርን መንፈስ ከእግዚአብሔር የሆነ መንፈስ የሚለው ጉዳይ

*እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል ከርሱም በሆነ መንፈስ ደግፏቸዋል።*
*አል-ሙጀደላህ(28)22*

በቅዱስ ቁርዓን የፍቺና ዝርዝር መጽሐፍ የሱፍ አሊ ብሎ የጻፈው እንዲህ ይነበባል «ከእርሱም በሆነ መንፈስ የሚለው መለኮታዊ መንፈስ ሲሆን በቂ በሆነ ሰብአዊ ቃል ትርጉሙን መስጠት የማይቻል ሲሆን ሊገልፀውም የሚችለው ሁሉ የእግዚአብሔር ማንነቱና ባህርይው ነው «የግርጌ ማስታወሻ ቁ 5365 እናም በቁርዓንም የምናየው ማስረጃ ሦስትዮሽ ማለትም የእግዚአብሔር፣ የእግዚአብሔር ቃል እና የእግዚአብሔር መንፈስ

ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ልዩ ሆኖም መለኮት ምስጢራቸው አንድ አይነት ፊፅሞም የማይለያዩ ናቸው።

ለማጠቃለል «ስላሴ» ወይንም «ሦስት አካላት» የሚሉትን ሀረጎች አትጠቀም ምክንያቱም ሙስሊሙ ጓደኛህ ሦስት አምላክ ያመልካል ብሎ እንዳይሸሽህ አስታውስ ሙስሊሞች አንድ እግዚአብሔር እርሱም አንድ ብቻ ነው የሚያስበው

ስለ ስላሴዎች ዝርዝር ዙሪያ ጥምጥም አትሔድ ሚስጥሩ ይቆይ እግዚአብሔር ራሱ እግዚአብሔር ይሁን። በቀላሉ ስለ እምነትህ ስትናገር አንድ አምላክ ብቻ እንደምታምን እርሱም ፈቃዱን በቃሉ አማካኝነት እንደገለፀና ይህንንም ደግሞ በመንፈስ እንዳደረገው መግለፅ ትችላለህ።

## 13. ኢየሱስ አምላክ አይደለም

የኢየሱስን ልዩ መሆን እና መለኮት መሆን ለሙስሊም ጓደኞቻቸው ለመመስከር ሲሉ ብዙ ክርስቲያኖች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው «ኢየሱስ አምላክ ነው» ይላሉ። ሆኖም የሚያመጣውን ውስብስብ ችግር ክርስቲያኖች አያስተውሉም። እስላም የአንድ አምላክ ሀይማኖት ነው። ለአንድ ሙስሊም አንድን ነገር ወይም ሠው አንድ አምላክ መቁጠር ሀይማኖትን መጣስ እና እጅግ አሳዛኝ ሐጢያት መሥራት ነው። ለዚህም ነው ቁርዓን ኢየሱስ ከአንዱ አምላክ ሌላ ለብቻው የሆነ እናም ሁለት አምላክ እንዳለ ያለውን ሀሳብ የሚቃወመው እንዲህ ሲል።

> *እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ አልመሲህም አለ: - የእስራኤል ልጆች ሆይ ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ እነሆ በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ መኖሪያውም እሳት ናት ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም።አል-ማኢዳህ 5/72/*

ለመመስከር የጋለ ፍላጐት ያላቸው ክርስቲያኖች ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ሲሉ ሙስሊሞች ሲሰሙ «ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል» «አባታችን እናም እርሱ አምላክ ከሆነ ክርስቲያኖች እንደሚሉት ክርስትና ቢያንስ ሁለት አማልክት ያመልካሉ ብለው ይደመድማሉ። ይህ ደግሞ እንዲሸሹ ያደርጋል።»

ክርስቲያኖችም ራሳቸውን ሊጠይቁ የሚገባቸው ነገር ቢኖር ሁለት አማልክት አለን ወይስ እንደ ሙስሊሞች አንድ አምላክ ብቻ ልክ ኢየሱስ እንዳስተማረው እናም ክርስቲያኖች መጠንቀቅ ያለባቸው ሙስሊሙ የተሳሳተ ግንዛቤ ላይ በመድረስ ከአንድ በላይ

አምላክ ያመልካሉ እንዳይል ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ነገር መልዕክቱ እጅግ ቀላል የሆነውን ወንጌልን ከመስማት የሚከላከለው የሚያሰናክለው እንቅፋት እንዳይኖር ኢየሱስም የአለም አዳኝ ሆኖ በመምጣት እና የእግዚአብሔርን ርህራሔ ለወደቀው የሰው ልጅ ለመግለፅ ከሀጢያት እርግማን ለመዋጀት እንደተገለጠ ማሳየት ነው፡፡

የኢየሱስን መለኮታዊ ባሕርይ የሚገልፁ ሀረጎችን በመጠቀም አንድ እውነት የሆነ አምላክ ያለ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ራሱን የገለፀው በኢየሱስ ውስጥ ነው፡፡ ለምሳሌ «የእግዚአብሔር ቃል» (ራዕ 19:13)፣ የእግዚአብሔር ክብር ነፀብራቅ እና ትክክለኛ የእርሱ ምሳሌ (ዕብ 1:3) የማይታየው አምላክ ምሳሌ (ቆላ 1:15) እና የእግዚአብሔር አምሳል (2ቆሮ 4:4) በመባል ይታወቃል፡፡

ስለ ኢየሱስ ተፈጥሮ ታላቅ ሚስጥር ለሙስሊም ዘርዝረህ ጨርሰህ መናገር ከአንተ አይጠበቅም፡፡ ማን ነው ከእኛ መካከል መለኮታዊ ሚስጥርን ጠንቅቆ የሚያውቅ? የወንጌልን ቀላል መልዕክት እንዳታወሳስብ ተጠንቀቅ እናም ትልቅ ጫና በሰዎች ላይ እንዳትጭን ጥንቃቄ አድርግ፡፡ በአዲስ ኪዳን በየትኛውም ክፍል ኢየሱስን ጠንቅቀን ባለማወቃችን ደህንነትን አናጣም፡፡ ደህንነት የተመሠረተው የኢየሱስን ጌትነት በሙሉ መግለፅ በመቻላችን ላይ ሳይሆን በኢየሱስ በማመን እና ለሰዎች ልጆች በእግዚአብሔር የተላከውን አዳኝ ከልብ መቀበል ነው፡፡ እርሱ ብቻ ከእግዚአብሔር የተላከ እርሱ ብቻ የሐጢያት ይቅርታና መዋጀትን የሚችል ነው፡፡ ይህ ነው የምሥራች፡፡

## 14. ኢየሱስ «የእግዚአብሔር ልጅ» አይደለም

መጀመሪያ ከሆኑት እውነታዎች አንዱ ሙስሊሞች ሊማሩ የሚያስፈልጋቸው ነገር የክርስትና ሀይማኖት እግዚአብሔር ሚስት አግብቶ ከተፀነሱ በኋላ የተወለደው ኢየሱስ ይባላል በሚለው ሀሳብ ላይ ነው፡፡ ምናልባት አንተ መፅሐፍ ቅዱስ እንደህ ያለ አስፀያፊ ነገር የለውም ልትል ትችል ይሆናል፡፡ በዮሐንስ 3:16 የተፃፈው ነገር ለሙስሊሙ ትልቅ ችግር ይፈጠርበታል፡፡ ይህንን ሲያነብ «አንድያ ልጁን እስኪሠጥ ድረስ» የሚለው ሀረግ ለሙስሊሙ ልዩ ትርጉም አለው፡፡ እግዜአብሔር ልጅ አለው ማለት በሙስሊሙ አስተሳሰብ የሚመጣው እግዚአብሔር ሚስት አለችው ማለት ነው፡፡

እርግጠኛ መሆን ያለብህ ከልጅነቱ ጀምሮ አንድ ሙስሊም አዕምሮውን የሚሞላ ቃል ቢኖር አላህ አንድ ነው እኩያም የለውም ረዳት የለውም ሚስት የለችውም አይወለድም አይወልድምም ሴት ጣያትም የለችም፡፡

> *(እርሱ) ሰማያትንና ምድርን ያለ ብጤ ፈጣሪ ነው ለርሱ ሚስት የሌላቸው ሲሆን እንዴት ለርሱ ልጅ ይኖረዋል? ነገርንም ሁሉ ፈጠረ እርሱም ነገሩን ሁሉ ነው፡፡*
>
> *አል-አንዓም (6)101*

*በል እርሱ አላህ አንድ ነው። አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። አልወለደም አይወለድምም ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።* *ኢኽላስ (112):1-4*

ምንም ያህል ሙስሊሞች የሚሁናከሉ ቢሆንም «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው ሀረግ ከመፅሐፍ ቅዱስ መሠረዝ አንችልም ሆኖም ለሙስሊሙ ምላሽ በጥንቃቄ መስጠት አለበት።

ከሁሉ በፊት ለሙስሊሙ ጓደኛህ ማስረዳት ያለብህ ነገር ይኸ ሀሳብ እንዳለ ጥሬ ቃሉን መውሰድ እንደሌለበት ነው። ቃሉ እግዚአብሔር ከሴት አምላክ ጋር ግንኙነት በማድረግ ወንድ ልጅ ወለደ ማለት እንዳልሆነ መንገር አለብን። ይኸ ሀሳብ ስዕላዊ ስለሆነ የተለያዩ ትርጉሞች እንዳሉት ንገረው:1 «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው በኢየሱስና እግዚአብሐር መካከል ያለውን ልዩ ግንኙነት የሚያሳይ ሊሆን ይገባል። በቀላሉ ሙስሊም ጓደኛህን ጥያቄ ጠይቀው እንዲህ ብለህ «በቁርዓን መሠረት የኢየሱስ እውነተኛ አባት ማነው?» ቁርዓን ኢየሱስ በተዓምር ከድንግል እንደተወለደ ስለሚናገር ምድራዊ አባት እንደሌላው ይረዳል። እናም «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው ኢየሱስ የትኛውም ወንድ ልጅ አለመሆኑን እንገነዘባለን። በአንፃሩ በቀጥታ እርሱ የመጣው ከእግዚአብሐር ነው።

«የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የእግዚአብሐር ተወካይና ሀይል ወራሽ መሆኑን ነው። የእግዚአብሔር ቃል የሚነግረን ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ሥልጣንን በመቀበል በግዛቱ ሁሉ ላይ ይሠለጥናል። ልክ ንጉስ ለወራሹ ስልጣኑን እንደሚያስረክብ እግዚአብሐርም ለወራሹ ስልጣንን በመስጠት መስፍን አረገው። እናም በንጉሱና በመስፍኑ የአባትና የልጅ ግንኙነት ነው። እንደ «የእግዚአብሔር ልጅ» ኢየሱስ የእግዚአብሔር ተወካይና የታላቅ ሀይሉና ሥልጣኑ ወራሽ ነው። በዚህ ምክንያት «የእግዚአብሔር ልጅ» በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የኢየሱስን መሲህነት ያሳያል። እንደ መሲህ ወይም እንደተቀባው ኢየሱስ ታላቅ መሪ በመሆን የጨለማውን ሀይል በመጣል ሕዝቡን ሁሉ ከክፉው አገዛዝ ነፃ ማውጣት ችሏል። ጴጥሮስም ለዚህ ነው። «አንተ መሲሁ የእግዚአብሐር ልጅ ነህ» ያለው።

«የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው ሀረግ መጠቀም ለሙተው ሞክር። በመጀመሪያ ሙስሊሞችን ስትቀርብ የተለያዮ የመፀሀፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለኢየሱስ ማብራሪያ ይሰጣሉ ለምሳሌ በሐዋሪያት ሥራ መፅሐፍ ውስጥ ሐዋሪያት ሲሰብኩ «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው የሚገልፀው ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ ስለነበረው መሲህ ነበር (9:20-22) በሐዋሪያት ሥራ የተለያዩ አገላለፆች አሉ። ለምሳሌ ጌታ እና መሲህ (2:36)፣ቅዱስና ፃድቅ (3:14)፣የሀይወት ራስ (3:15)፣ ቅዱስ ብላቴና (4:27)፣አዳኝና ገዥ (5:31)፣ የሰው ልጅ

(7:36)፣ የሁሉም ጌታ (10:36)፣ የህያዋንና ሙታን ፈራጅ (10:42)፣አዳኝ (13:23) እና ክርስትስ (18:5) ናቸው።

_ ለማጠቃለል ኢየሱስን ለሙስሊም ለመመስከር ስታስብ እግዚአብሔር ስለሠጠው ትልቅ ሥልጣንና ሀይል ተናገር። የእግዚአብሔር ቅዱስ ብላቴና እንደሆነ የሠዎችን ልጆች ለማገልገል እና ስለሁሉ ነፍሱን ለመስጠት መምጣቱን ተናገር። የሰላም አለቃ ሠላምን በአለም ላይ ለመመስረትም እንደሚመጣ ግልጽ አርገህ አስረዳ ከሠይጣን ሥራ እና ከሀጢያት ርግማን ይኸችን አለም ለማዳን ወደዚህ አለም እግዚአብሔር እንደላከው አስተምር ቅዱስና ፃድቅ የሆነ በእርሱም ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ የዘላለም ህይወት እንደሚወርሱ ተናገር።

## 1.5.ኢየሱስ መመለክ አይገባውም

ብዙ ሙስሊሞች የኢየሱስን በክርስቲያኖች መመለክ በፅኑ ይቃወማሉ። የሚከራከሩት አላህ አንድ ሊመለክ የሚገባው አንድ አላህ ብቻ ነው በማለት ነው ለሌላ ፍጡር መስገድ ሽሪክ - እጅግ የከፋ ሀጢያት ነው እንደሙስሊሙ ይሁን እንጂ ቁራዓንም ራሱ አላህ መላዕክትን ከእርሱ ውጪ ስለሆነ ለሌላ እንደይሠገድ እንዳዘዘ ያስተምራል። ለአደም እንደይሠግዱ አዘዛቸው።

- *ለመላዕክትም ለአደም ስገዱ ባልን ጊዜ ( አስታውስ) ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ ኢብሊስ (ዲያብሉስ) ብቻ ሲቀር እምቢ አለ ኮራም ከከሐዲዎችም ኮነ።* ሴል-በቀራህ (2):34

*ጌታህም ለመላእክት ባለ ጊዜ (አስታውስ) እኔ ሰውን ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማ ጭቃ እፈጥራለሁ ( ፍጥረቱን) ባስተካከልኩትና በውስጡ ከመንፈሴም በነፋሁበትም ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ሁናችሁ ውደቁ።* ሒጅር (15) : 28-29

_ ስለዚህ አላህ ሁሉን አዋቂ ያለፈውን ያለውን እና የሚመጣውን የሚያውቅ አሁንም መላዕክትን በመጀመሪያው ሰው አዳም ፊት እንዲሠግዱ ያዛል ለሙስሊሙ ቅዱሳት መፃህፍት ስለ ሌላ «አዳም» እንደሚናገር መጠቆም ይጠቅማል። ልክ ለፊተኛው ለአዳም ሀይልና ሥልጣን ምድርን እንዲገዛ እግዜአብሔር እንደሾመው ሁሉ ለሁለተኛው አደም ሀይልና ሥልጣን በሰማያዊው ግዛት ሁሉ ተሰጠው ይህ ሌላው አዳም «ሁለተኛው» ወይም «የመጨረሻው» አደም በመባል ይታወቃል። እርሱም መሲሁ ኢየሱስ ነው። የመጀመሪያው አደም ከመሬት ሲሆን ሁለተኛው አደም ግን ከሠማይ ነበር።

*ስለዚህ የመጀመሪያው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተፅፏል የኋለኛው አደም ግን ሕይወትን የሚሠጥ መንፈስ ሆነ። መንፈሳዊው ሳይሆን ፍጥረታዊው*

*ነው ከዚያም በኋላ መንፈሳዊው መጣ:: የመጀመሪያው ሰው ከምድር የተገኘ ምድራዊ ነው የኋለኛው ግን ከሠማይ ነው::* *1ቆሮ 15:45-47*

ከላይ በተመለከትነው ክፍል ሁለተኛው አዳም እርሱም ኢየሱስ የሰዎችን ልጆች ሁሉ ወደ ዘላለማዊ እና መንፈሳዊ የእግዜአብሔር ህልውና ለመመለስ ሀይልና ሥልጣን አለው ይህም አዳም በሰይጣን ተታሎ ከመውደቁ በፊት የነበረበት ቦታ ነው:: ለሚከተሉት ሁሉ ኢየሱስ ያንን መንፈሳዊ እና ዘላለማዊ ህይወት የመስጠት ሙሉ ስልጣን አለው:: ቃሉም ይህንኑ ይላል::

*ከአንተ ለተቀበላቸው ሁሉ የዘላለምን ህይወት እንዲሠጥ በሰው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥተኸዋልና እውነተኛ አምላክ የሆንከውን አንተንና የላከኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት::* *ዮሐ 17:2-3*

*ቁርዓንም ኢየሱስ በዚህና በወዲያኛው አለም የተከበረ እንዲሆን ያስተምራል:: ሙስሊሞች ለመሲሁ ለኢየሱስ የተሠጠውን ክብር ከቁርዓን በማንበብ ይረዳሉ:: ለምፅን መፈወስ፣ዕውር ማብራቱ፣ሙታንን ማስነሳቱ ፣መፍጠሩ ሳይቀር የሚየረጋግጠውን ይመለከታሉ::* *(ኢምራን (3):49)*

*አላህ ከእርሱ በሆነው ቃል ስሙ አልመሲህ ኢሳ የምርያም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ ከባለሟሎችም በሆነ (ልጅ) ያበስርሻል::*
*አል -ኢምራን (3) 45*

የሚያሳዝነው ብዙ ሙስሊሞች ለኢየሱስ የተሰጠውን ታላቅ ክብር አለማወቃቸው ነው:: የሚከተለውን ክፍል ለሙስሊሙ እንብብለት::

*ይህን ኢየሱስ እግዚአብሔር ከሞት አስነሳው እኛም ሁላችን ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ካለ በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ከአብ ተቀብሎ አሁን የምታዩትንና የምትሠሙትን አፈሰሰው::* *ሐዋ ሥ 2:32-33*

*ሰው ሆኖ ተገልጦም ራሱን ዝቅ አደረገ እስከሞት ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ:: ስለዚህ እግዜአሔር እጅግ ያለልክ ከፍ ከፍ አደረገው ፣ ከስምም ሁሉ በላይ ያሆነውን ስም ሠጠው ፣ ይኸውም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉትን ሁሉ ለኢየሱስ ይንበረከክ ዘንድ ምላስም ሁሉ ለእግዜአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሥክር ዘንድ ነው::* *ፊል 2:8-11*

*ኢየሱስም ስለራሱ ለደቀመዛሙርቱ ሲናገር ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሠጠኝ::* *ማቴ 28:18*

ለዚህ ሀይልና ሥልጣን ለተሠጠው በመስቀል ላይም ራሱን በመሠዋት ለታዘዘው «ለእግዜአብሔር በግ» የመላዕክት አዕላፋት ሲያመልኩት: -

*ከዚያም ተመለከትሁ የብዙ መላዕክትን ድምፅ ሰማሁ ቁጥራቸውም ሺህ ጊዜ ሺህና እልፍ ጊዜ እልፍ ነበር እነርሱም በዙፋኑና በሕያዋን ፍጡራኑ በሽማግሌዎቹም ዙሪያ ከበው ነበር በታላቅ ድምፅም እንዲህ ብለው ዘመሩ «የታረደው በግ ኀይልና ባለጠግነት ጥበብና ብርታት ክብርና ሞገስ ምስጋናም ሊቀበል ይገባዋል::»* *ራዕ 5:12-13*

በዚህ ውስጥ ሁሉ እግዚአብሔር የነገሥታት ንጉሥ እና የጌቶች ጌታ አድርጎ ለቀባው (ራዕ. 19:16) እኛ ሟች የሆንን ፍጡራን አንሰግድም ለማለት እንደፍራለን? ልክ አብዛኞቹ ሙስሊሞች የእግዚአብሔር ቃል አድርገው የሚያከብሩትን ቅዱስ መጽሐፋቸውን እንደሚስሙ፣ እውነተኛ ክርስቲያኖችም እንደፍጡር ያልተፈጠረውን እና ዘላለማዊ የሆነውን፣ እንዲሁም ህያው የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን የኢየሱስን እግሮች ይስማሉ:: ስለዚህም ለሌላ አምላክ እንደማትሰግዱ ወይም ለኢየሱስ የሰብዓዊ ተፈጥሮ እንደማትሰግዱ፣ ነገር ግን የ«እግዚአብሔር ቃል» መሆኑን ለሚገልፀው ለመለኮታዊ ባህርይው እንደምትሰግዱ ለሙስሊም ወዳጃችሁ መግለፅ እጅግ አስፈላጊ ነው:: በቁርአን ታሪክ ውስጥ፣ መላዕክት ከሸክላ አፈር ለተሠራ ሰው መስገዳቸው ተገልጿል፣ በእውነተኛ ክርስቲያናዊ ልምምድ ግን አማኞች የሚሰግዱት የእግዚአብሔር ቃል ለሆነው፣ የማይታየው አምላክ ምሣሌ ለሆነው፣ ከእግዚአብሔር ለማይለያየው እንዲሁም ከዘላለም እስከዘላለም እውነተኛ መለኮታዊ ባሕርይ ላለው ጌታ ነው!

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ፣ አብዛኛውን ጊዜ ሙስሊሞች ወደ ኢየሱስ ስለመፀለይ ተግባር ክርስቲያኖችን ይጠይቃሉ:: ነገር ግን ደቀመዛሙርቱ በስሙ ዕርዳታ ከጠየቁ፣ የጠየቁትን እንደሚሰጣቸው ያስተማራቸው ኢየሱስ ራሱ ነበር:: ስለዚህ እውነተኛ የኢየሱስ ተከታዮች የሆኑት አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ኢየሱስ በአሁኑም ዘመን ሕያው እንደሆነ እና በመንግሥተ ሰማያት ውስጥ በአብ ቀኝ እንደተቀመጠ፣ ስሙን ለሚጠሩ ደግሞ ፍፁም ነፃነት እና ደህንነት ለመስጠት መብትና ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን በማወቅ ወደ ኢየሱስ ይፀልያሉ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ብሩክ ለሆነው ለኢየሱስ የተሰጠውን ታላቅ ክብር እና ሥልጣን በፍፁም መልሶ አልወሰደም:: ኢየሱስ የዲያብሎስን ሥራ ሲያፈርስ ወደ ሰብዓዊነት ልምምዶች ውስጥ እንደገባ ቅዱሳት መጽሐፍት በግልፅ ይመሰክራሉ:: በመሆኑም የሚጠሩትን ሁሉ በእርግጠኝነት ይረዳቸዋል::

> *«እኔም /ኢየሱስ/ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ::*
> *ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ::»*
>
> ዮሐ. 14:13-14

## 16. ኢየሱስ አልተሰቀለም ነበር

ምናልባት አብዛኞቹ ሙስሊሞች የአዲስ ኪዳንን እውነት እንዳይቀበሉ ትልቅ እንቅፋት የሆነባቸው የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሰቀል ታሪክ ሊሆን ይችላል:: ኢየሱስ በመስቀል ላይ የመሞቱን የተረጋገጠ እውነታ በሃሳብ ግትርነት የማይቀበሉ ሲሆን፣ ጠቅላላው የስቅለቱ ታሪክም የክርስቲያኑን ማህበረሰብ ለማሳሳት የተፈጠረ የማታለል ድርጊት ነው

በማለት ድርቅ ይላሉ። በተጨማሪም እነዚሁ አብዛኞቹ ሙስሊሞች ቁርአን የተገለፀበት አንዱ ምክንያት ይህንኑ «ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞቷል» የሚለውን የሐሰት ትምህርት ለማረም ነው ይላሉ።

እንግዲህ የስቅለቱ ታሪክ ሐሰት ከሆነና ቁርአንም የመጣው ይህንኑ የሐሰት ትምህርት ለማረም ከሆነ፣ በእርግጥም ቁርአን የሙታን ትንሣኤን እና የፍርድ ቀንን የሚያውጁ በርካታ ጥቅሶች እንዳሉት ያህል፣ «ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም» የሚለውንም የሚያውጁ በጣም በርካታ ጥቅሶች ይኖሩታል ብሎ መጠበቅ ተገቢ ነው። ቁርአን ከ6000 ጥቅሶች በላይ ስላሉት ከእነዚህ ሁሉ ጥቅሶቹ ውስጥ በቀላሉ 5 ፐርሰንቱ እንኳ «ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም» እንደሚል መጠበቅ ብዙ መጠበቅ ይሆንን? ደግሞስ 1 ፐርሰንት ያህል መጠበቅስ? ይህ ማለት ከጠቅላላው የቁርአን መጽሐፍ ውስጥ ስልሣ ጥቅሶች ብቻ ይኖራሉ ማለት ነው። ቢያንስ ከ6000 ጥቅሶች ውስጥ «ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም» የሚሉ 10 ግልጽ የሆኑ ጥቅሶችን ልንጠብቅ እንችላለን። ይህ ከሆነ በእርግጥም ይህንን ክርክር ግልፅ የሚያደርገው ይሆናል፣ አብዛኞቹ ሙስሊሞችም ቁርአን የሚናገረውን የሚደግፉ ቢያንስ 10 ጥቅሶች ሊኖሩት ይገባል በማለት ይስማማሉ።

አሁን አስደናቂውን መግለጥ እንይ! ከ6000 የቁርአን ጥቅሶች ውስጥ ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም ወይም አልተሰቀለም የሚል በቀላሉ የሠፈረ ጥቅስ እንኳ የለም። አንድም የለም! ከዚህ በተጨማሪ በቁርአን ውስጥ ሁሉ ስለስቅለቱ ጉዳይ የሚናገር አንድ ምንባብ ብቻ ይገኛል። እንዲህ ይነበባል:-

> እኛ የአላህን መልእክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሣን ገደልን በማለታቸውም (ረገምናቸው)፣ አልገደሉትም፣ አልሰቀሉትምም፣ ግን ለእነሱ (የተገደለው ሰው በዒሣ) ተመሰለ፣ እነዚያም በእርሱ ነገር የተለያዩት፣ ከእርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፣ ጥርጣሬ ከመከተል በስተቀር በእርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፣ በእርግጥም አልገደሉትም።
>
> ሱረቱ-አል ኒሳእ /4/:157

ምንባቡን በጥንቃቄ ተመልከቱ። የምንባቡ ርዕስ ኢየሱስ ሳይሆን አይሁዳውያን ናቸው። አይሁድ ኢየሱስን እንዳልገደሉ ወይም እንዳልሰቀሉም በግልጽ ይናገራል። በየትም ቦታ ላይ ግን «ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም» ሲል አይናገርም። ስለስቅለቱ የሚናገረው ይህ ጥቅስ ብቻ ነው።

«ለእነርሱ ግን የሞተ መሰላቸው» የሚለው ሐረግም ግልጽ አይደለም፡፡ በዚህ ምክንያት ኢየሱስ ከመስቀል ሞት ለምናልባቱ የዳነበት ሁኔታ ለበርካታ የሚስቡ ቲዮሪዎች በር ከፍቷል፡፡ አንደኛው ተመራጭ ባህልና ወግ የሚለው እግዚአብሔር የከሃዲውን የይሁዳን መልክ እንደ ኢየሱስ አስመስሎ ስለለወጠው በመስቀል ላይ የተቸነከረው ኢየሱስ ሳይሆን ይሁዳ ነበር፣ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ታሪክ ግን በየትኛውም የቁርአን ምንባብ ውስጥ አይገኝም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ታሪኮች የሚመጡት ከታላላቅ ታሪክ ተራኪዎች ምናብ ብቻ ነው፡፡

ይህ በጥያቄ ምልክት ውስጥ ያለው ሐረግ በዚህ መንገድም ሊገለጽ ይችላል፡፡ ይኸውም፣ አይሁድ በኢየሱስ ላይ ሤራ ጠንስሰው ሙሉ በሙሉ እንዳጠፉት ፎክረው ነበር፡፡ ዕቅዳቸው ግቡን እንደሖታ እና የኢየሱስ አገልግሎትም የታፈነ መሰሏቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔርም እያቀደ ነበር፡፡ ምንም እንኳ ኢየሱስ ቢሞት፣ እግዚአብሔር ግን በእርግጥም ኢየሱስ መሲህ እንደነበር ለአይሁዳውያን ሊያስረዳ በህይወት አስነሳው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር የዓለም አዳኝ እና ገዥ አድርጎ ቀብቶት ነበርና ነው፡፡

እንደቅዱሳት መፃህፍት አገላለጽ፣ ኢየሱስ የመስቀል ላይ ስቃይና መከራን መቀመሱ የእግዚአብሔር መልካም ዕቅድ ነበር፡፡ ይህ የኢየሱስ ሞት፣ እግዚአብሔር እንዲያመልኩት እና እንዲያወድሱት በፍቅሩ የፈጠራቸው የሰው ዘሮች ሳይቋረጥ በሚያሳዩት ኃጢአት እና ዓመጽ የተነሳ እግዚአብሔር የደረሰበትን የፍቅር ስቃይ የሚገልፅ ነበር፡፡ ከዚሁ ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር በተያያዘ፣ የኢየሱስ ሞት ራሱ የሁሉም የእንስሳት መስዋዕትነት ማሚያ እና ፍፃሜ ነበር፡፡ «የእግዚአብሔር በግ» ተብሎ የተጠራበት ምክንያትም ይህ ነው፡፡ የእርሱ መስዋዕትነትና የኃጢት ሥርየት ሞቱ የተፈፀመው የኃጢአት ይቅርታን እና መቤዠትን ለመስጠት፣ ከሁሉም ጠቃሚው ደግሞ እግዚአብሔር ወደሚኖርበት ሥፍራ የሚያስገባውን መንገድ ለመክፈት ነበር፡፡ ሰውን ወደ እግዚአብሔር መኖሪያ የሚመራው እየሱስ እንጂ፣ ባለአራት እግር የመስዋዕት እንስሳ አልነበረም! አስቀድሞ ይቀርብ የነበረውም የእንስሳት መስዋዕትነት ወደፊት እግዚአብሔር የሚያቀርብውን እጅግ ንፁህ መስዋዕት የሚያሳይ ምልክት ብቻ ነበር፡፡

ስለዚህ ይህ ሁሉ ዕቅድ የእግዚአብሔር እንጂ የአይሁዳውያን ዕቅድ አልነበረም፡፡ ኢየሱስን በመስቀል ላይ የሰቀሉት አይሁዳውያን ሳይሆኑ፣ ነገር ግን ለሰው ዘር በሙሉ የማዳን ዕቅዱን ሊገልጽ የፈለገው እግዚአብሔር ነበር፡፡ የመስቀሉ ተግባር የሰይጣንን ዘዴ እና ዕቅድ ድል ለመንሳት የተከናወነ መሆኑን ለዓለም ለማስረዳት፣ እግዚአብሔር

ኢየሱስን ከሞት አስነስቶ በክብር ወደ መንግስተ ሰማያት ከፍ ከፍ በማድረግ በዙፋኑ በስተቀኝ አስቀመጠው!

ቁርአን የኢየሱስን ሞት በሚከተለው ሁኔታ ይገልፃል:: ይኸውም፣

> ሰላምም በእኔ ላይ ነው በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን ህያው ሆኜ በምቀሰቀስበትም ቀን፣
>
> ሱረቱ መርየም /19/:33

አብዛኞቹ ሙስሊሞች የኢየሱስን መወለድ እና ወደ መንግስተ ሰማያት መወሰዱን ይቀበላሉ:: ይህም በመሆኑ ከላይ በሠፈረው የቁርአን ጥቅስ እንደተገለፀው፣ ኢየሱስ በመካከሉ በነበረው አንድ ቦታ ላይ መሞቱን ለማመን በጣም ሊያስቸግራቸው አይገባም:: ምክንያቱም ይህ ጥቅስ ኢየሱስ መወለዱን፣ ከሞት መነሳቱን እና ወደ ሰማይ ማረጉን ከሚያስተምረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር በደምብ ይስማማል:: እንደ አለመታደል ግን፣ ቁርአን ኢየሱስ እንዴት እንደሞተ አይነግረንም:: በእርግጥ ይህ ሁኔታ ጥያቄ የሚፈጥር ሲሆን፣ ቁርአን ራሱም አንድ ሰው ጥርጥር ሲሰማው የሚከተለውን /መመሪያ/ በግልጽ ያስቀምጣል::

> ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መፅሀፉን የሚያነቡትን ጠይቅ፣ እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሀል፣ ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን:
>
> ሱረቱ ዩኑስ /10/:94

መጽሐፍ ቅዱስ ግን መልሱን በጣም ግልጽ አድርጐ ስለሚሰጥ ኢየሱስ እንዴት እንደሞተ *«የመጽሐፉ ሰዎች»* በሚገባ ያውቃሉ:: የሚከተሉት ጥቅሶች ከማንኛውም ጠያቂ ግለሰብ አእምሮ ውስጥ የሚነሳ ጥርጣሬን ማስወገድ አለባቸው::

> «ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሊወጣ ሳለ፣ በመንገድ አስራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ብቻቸውን ወደ እርሱ አቅርቦ:- እነሆ፣ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣን፣ የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለፃፎች ይሰጣል፣ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፣ ሊዘባበቡበትም፣ ሊገርፉትም፣ ሊሰቅሉትም ለአህዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፣ በሦስተኛውም ቀን ይነሳል አላቸው»
>
> ማቴ.20:17-19



62

«የእስራኤል ሰዎች ሆይ፣ ይህን ቃል ስሙ፣ ራሳችሁ እንደምታውቁ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሐር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበር፣ እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው ሃሣቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በአመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሳው፣ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና።»

የሐዋ.ሥራ 2:22-24

## 17. የዓሣማ ሥጋ መብላት ሕገ ወጥ ድርጊት ነው

ክርስቲያኖች በነፃ ስሜት የዓሣማ ሥጋ ሲበሉ የሚመለከቱ ሙስሊሞች ድንጋጤ ይይዛቸዋል። እስካሁን ድረስ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አይሁዳውያንን ሕይወት መንካት እንደቀጠለው እና በሕገ-ሙሴ ሥር እንደነበሩት የጥንት የእስራኤል ልጆች እነርሱም ዓሳማ ሲመለከቱ ይፀየፋሉ። በእርግጥ ዓሳማ መብላት በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ በግልጽ የተከለከለ ነው። ይኸውም:-

«መናውም እንደድንብላል ዘር ነበር፣ መልኩም መጫ ይመስል ነበር። ሕዝቡም እየዞሩ ይለቅሙ ነበር፣ በወፍጮም ይፈጩት ወይም በሙቀጫ ይወቅጡት፣ በምንቸትም ይቀቅለት ነበር፡ እንጐቻም ያደርጉት ነበር።»

አሪት ዘኁልቁ 11:7-8

ተመሣሣይ የክልከላ ትዕዛዝም በቁርአን ውስጥ ይገኛል።

በእናንተ ላይ እርምም ያደረገው በክትንና ደምን የእሪያ ሥጋንም በእርሱም (ማረድ) ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ነገር ብቻ ነው፣

ሱረቱ- አል-በቀራህ /2/:173

በእስላም ኃይማኖት ውስጥ የዓሣማ ሥጋ መብላት በጥብቅ የተከለከለ ስለሆነ ሙስሊሞች የዓሳማን ሥጋ መብላት እጅግ እርኩስ የሆነ እና በእግዚአብሔር ፊት የሚፈፀም አስፀያፊ ተግባር አድርገው ይመለከቱታል። ከዚህ የተነሣ የቅዱሱ ነቢይ የኢየሱስ ተከታዮች ነን የሚሉ ሕዝቦች የዓሣማ ሥጋ መብላታቸው ግልፅ ተቃርኖ እና ተፃራሪ ነገር እንደሆነ ያስቡታል።

በመሆኑም የሕገ-ሙሴን ባህርይ እና ለእስራኤል ልጆች የነበረውን የተለየ ዓላማ ለሙስሊሞች መግለፁ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን ሕግ የሞራል እና የሲቪል ሕግጋትን አጣምሮ ይይዛል። የሞራል ሕጉ የሕይወትን ትልቅ ሥነ ምግባር የሚዳስስ ሲሆን፣ ዓላማውም ለእግዚአብሔር እና ለሰብዓዊ ፍጡሮች ክብር በሚያስገኝ ሁኔታ በውስጣዊ ቅድስና ላይ ተመስርቶ የተመረጠውን የ«እስራኤል ሕዝብ» ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ ለመለየት ነው። ይህ ትልቅ የሞራል ሕግ የእስራኤል ልጆች ወደ ከፍተኛው የቅድስና ደረጃ እንዲያደርሱ እና በዘመናት ሁሉ ለሚፈጠሩ ሕዝቦች ምሣሌ ሆነው እንዲያገለግሉ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ አስርቱ ትዕዛዛት ሰዎች ለእግዚአብሔር እና ለሌሎች ሰዎች ካለባቸው ኃላፊነት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ግብረ ገባዊ ሕግና ደንብ ነው። እነዚህ ሕግጋት በሕዝቦች ስሜትና አመለካከት /ኢንቫይሮንሜንት/ ለውጥ የተነሳ ተጽእኖ የማይደርስባቸው ሕግጋት ስለሆኑ ሳይለወጡ የሚኖሩ ናቸው።

የሲቪል ሕጉ ግን የተለየ ነበር። ምክንያቱም ከዕለታዊ ሕይወት ጋር በቀጥታ የሚገናኙ መመሪያ እና ደንቦችን የያዙ ሲሆን፣ እነዚህ መመሪያዎች ግን በሕዝቦች ስሜትና አመለካከት እንዲሁም በአቅራቢያ በሚኖሩ ሕዝቦች ወግና ልማድ ጫናና ተጽእኖ የነበረባቸው ነበሩ። እነዚህ ህግጋት የንጽህናን፣ የአመጋገብን የጤና አጠባበቅን፣ የአለባበስን እና የኃይማኖታዊ ሥርዓት ጉዳዮችን የሚዳስሱ ስለነበር፣ የሕግጋቱ ዓላማ የእስራኤልን ልጆች በውጫዊ ቅድስና ላይ በተደገፈ መልኩ ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ ለመለየት ነበር። የእስራኤል ልጆች የተለዩ እና ልዩ ሆነው የሚቀሩ፣ እንዲሁም እውነተኛ የሆነውን አንድ አምላክ የሚያመልኩ እና በዙሪያቸው የከበባቸውን የጣዖት አምልኮ ልምድና ጕታች ባህል ተቀብለው ለማስተናገድ እምቢተኞች ስለነበሩ፣ በተቀረው የዓለም ሕዝብ ፊት ሊጠፉ የተዘጋጁ ነበሩ።

ከእነዚህ የሲቪል ሕጐች መካከል የዓሣማ ሥጋ መብላትን የሚከለክል ሕግም ነበር። በአቅራቢያ ያሉት ጣኦት አምላኪ ሕዝቦች ግን ዓሣማን እንደቅዱስ መስዋት አድርገው ለጣዖቶቻቸው ማቅረብ የለመዱት ተግባር ነበር። ከዚህ በተጨማሪ፣ በዚያን ወቅትን እና በዚያ የዓለም ክፍል ውስጥ «ዓሣማ» የሞተ እንስሳትን ሥጋ እና ቆሻሻዎችን የሚለቃቅም ልክስክስ እንስሳ ስለነበር ሥጋውን መብላት መላውን ህብረተሰብ የጉዳ አስፈሪ በሽታ አስፋፍቶ ነበር። የእስራኤል ልጆች ግን ከእንዲህ ዓይነቱ የጣኦት አምልኮ ተፅእኖ እና ፀያፍ ነገር ራሳቸው የሚለዩ ነበሩ።

የእስራኤል ልጆች ቅዱስ ሕዝብ እንዲሆኑ የተመረጡ፣ ራሳቸውን አንድና እውነተኛ አምላክ ለሆነው ለአብርሃም፣ ለይስሐቅ እና ለያዕቆብ አምላክ ያስገዙ ሕዝቦች እንደነበሩ



64

ለሙስሊሙ ማስታወስ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ይህን ሕዝብ በጣም ልዩ ለሆነ ምክንያት ከሌሎች ሕዝቦች ልዩ ማድረጉ፣ ለተቀረው ዓለም የማያቋርጥ አስታዋሽ እንዲሆን ነበር። ቁርአን ጭምር ስለዚህ ጉዳይ የሚለው አለው። ይኸውም፦

> ባሮቻችንንም ኢብራሂምን፣ ኢስሃቅንና ያዕቆብንም የኃይልና የማስተዋል ባለቤቶች የሆኑትን አውሳላቸው። እኛ ጥሩ በሆነች ፀባይ መረጥናቸው፣ (እርሷም) የመጨረሻይቱን አገር ማስታወስ ናት።
>
> ሱረቱ-አል ሷድ /38/45:46

> የእስራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በእናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋየንና እኔም በዓለማት ያበለጥኳችሁ (1) መሆኔን አስታውሱ።
>
> ሱረቱ-አል-በቀራህ /2/:47

የእስራኤል ልጆች ለምን በጣም ልዩ እንደነበሩ እና እግዚአብሔርም የመረጣቸው ለምን ዓላማ እንደነበር ለሙስሊም ወዳጅዎ ይግለፁ። እኛ ግን፣ ይህ ህብረተሰብ የተመረጠው፣ የሰውን ዘር ለማዳን እና ለመቤዠት ከእግዚአብሔር የተላከው ቅዱስ የዓለም አዳኝ መሢሁ ኢየሱስ የሚመጣበት መንገድ መሆኑን አሁን ተገንዝበናል። የእግዚአብሔር ቃል በኢየሱስ ማንነት በኩል እንደሰው ሥጋ ለብሶ ከድንግል ማርያም ተወልዷል። ይህም ቅዱስ አዳኝ ከእስራኤል ልጆች መካከል ከአብርሃም፣ ከይስሐቅ፣ እና ከያዕቆብ ዘሮች የሚወለድ ስለነበር፣ እነዚህ ሕዝቦች ቅዱስ መሆናቸው እና ከሌሎች ሕዝቦች ተለይተው መጠራታቸው የሚያስገርም ነገር የለበትም።

እንደአለመታደል ግን፣ ኢየሱስ በምድር ላይ በሚያገለግል ጊዜ ከእስራኤል ልጆች መካከል አብዛኞቹ የሲቪል ሕጉን ዓላማ ዘንግተው ስለነበር የእጆችን መታጠብ እንደልብ መታጠብ አድረገው በመተካት በዕለታዊ የሲቪል ሕጎች መመሪያ እና ደንብ ላይ ይበልጥ ትኩረት ማድረግ ጀመሩ። እንዲያው የሃይማኖት መሪዎቹ በርካታ ደንቦችን ከራሳቸው በመጨማመር በትክክል ለመጠበቅ በጣም አስቸጋሪ ከሆነው የልብ ንፁህና ጋር በሚቃረን ሁኔታ «እውነተኞቹ የቅድስና ደረጃዎች እነዚህ ናቸው» አስከማለት ደረሱ። በዚህ የተነሳ ለብዙዎቹ ህዝቦች እውነተኛው ኃይማኖት በትምክህትና በግብዝነት ወደ ታጠረ በድን ኃይማኖታዊ ሥርዓት ዝቅ አለ። እነዚህ የኃይማኖት መሪዎች በውጫዊ ማንነታቸው ፀሎታቸውን ሲደግሙ፣ እጆቻቸውን ሲታጠቡ እና የተፈቀዱ ምግቦችን ብቻ ሲመገቡ ይታያሉ። በውስጣዊ ማንነታቸው ግን፣ ልባቸው



69

በጥላቻ እና ስግብግብነት፣ በምኞት እና በቅናት በሽታ ተለክፎ ነበር:: ሰዎችም ሕጉን በማጣመም ስለራሳቸው ቅድስና ጉራ ለመንዛት ያለአግባብ ተጠቅመውበት ነበር!

በመሆኑም ኢየሱስ ይህንን የሲቪል ሕግ ሰብዓዊ ፍጡራን ያለአግባብ እንዳበላሹ ተመልክቶ እግዚአብሐር በሰጠው ሥልጣን መሠረት ተገቢውን እርምጃ ወሰደ:: ይህን ዓይነቱን ግብዝነት እና መመፃደቅ ለማስወገድና የእውነተኛ ቅድስናን ትኩረት ወደልብ ለመመለስ ሁሉም ዓይነት ምግብ ንፁህ መሆኑን ገለፀ:: በዚህ ደግሞ ሁሉም ምግብ ተገቢና ሕጋዊ እንደነበር ለኢየሱስ ተከታዮች ታወጀ:: ቁርአን ኢየሱስ የተናገረው ነው በማለት ሲጠቅስ እንዲህ ይላል::

> «ከተውራትም ከኔ በፊት ያለለውን ያረጋገጥሁ ስሆን የዚያንም መእናነተ ላይ እርም የተደረገውን ከፊል ለእናንተ እፈቅድ ዘንድ (መጣኋችሁ)...»
>
> ሱረቱ አሊ-ዒምራን /3/:50

በአዲስ ኪዳን ውስጥም ኢየሱስ ስለቅድስና የሰጠውን ትምህርት እናነባለን::

> «እርሱም:- እናንተ ደግሞ እንደዚህ የማታስተውሉ ናችሁን? ከውጭ ወደ ሰው የሚገባው ሊያረክሰው ምንም እንደማይችል አትመለከቱምን? ወደ ሆድ ገብቶ ወደ እዳሪ ይወጣል እንጂ ወደ ልብ አይገባምና፣ መብልን ሁሉ እያጠራ አላቸው:: እርሱም አለ:- ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ያ ነው:: ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ ሃሣብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጐምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ስድብ፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸውና፣ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውን ያረክሰዋል::»
>
> ማርቆስ 7:18-23

በተጨማሪ መጠቀስ ያለበት እውነት ኢየሱስ ወደ ዓለም ከመምጣቱ የተነሳ፣ ከእንግዲህ የእስራኤል ልጆች ሙሉ በሙሉ የተለዩ ህብረተሰቦች ሆነው መዝለቅ አያስፈልጋቸውም:: እንዲያውም ኢየሱስ የመጣው ሁሉንም የዓለም ባህሎች ለእግዚአብሔር ለማስተባበር እና የሰው ዘሮች ሁሉ በታላቁ የእግዚአብሔር ሞራላዊ የቅድስና ሕግጋት እንዲኖሩ ኃይልና ሥልጣን ለማስታጠቅ ነው:: ይህ ህብረተሰብ በዓለም ሁሉ እየተንሰራፋ ሲሄድ፣ የሕዝቦችን ስሜት እና አመለካከት እንዲሁም የሰውን ሕይወት በማነኩ የለውጥ

ክስተቶች የተነሳ ግዙፍ ልዩነቶች ስለሚኖሩት፣ ለሁሉም በጋራ የሚሆኑ የሲቪል ሕጎች እንደሌሉ በግለፅ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ የኢየሱስ ትልቁ የግብረ ገብ ትምህርት ለሁሉም ሕዝቦች ሳይለወጥ የሚኖር ነው:: ይኸውም ለሁሉ ቻይ አምላክ ትልቅ ክብር የሚያመጣው ከምግብ መቆጠብ ሳይሆን፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር እና ለፍጡር ወገናችን የምንገልፀው እውነተኛ ፍቅር ነው::

በተጨማሪ መታወስ ያለበት የሙሴ ሕግ የተሰጠው ለእስራኤል ልጆች ስለነበርና አብዛኞቹ ክርስቲያኖችም የእስራኤል ዝርያዎች ባለመሆናቸው ለማህበረሰብ ልምድና ምግባር ለተሰጡ የሲቪል ሕጎች የሚገዙ አይደሉም::

ነገር ግን ክርስቲያኖች የዓሣማ ሥጋ ከመብላት የሚቆጠቡባቸው ጊዜያት አሉ:: እነርሱ ባሉበት የዓለም ክፍል አካባቢ ዓሣማዎች የሚመገቡት የሬሣ ሥጋ እና ጥንብ ነገሮችን ከሆነ፣ ለጤና አጠባበቅ ምክንያቶች ሲሉ የዓሣማ ሥጋ ከመብላት ይጠነቀቃሉ:: በተጨማሪ የዓሣማ ሥጋ መብላት ለሙስሊም ወዳጆቻቸው እና ጐረቤቶታቸው በሚያደርጉት ምስክርነት ላይ እንቅፋት ይፈጥራል ብለው የሚያስቡ አንዳንድ ክርስቲያኖችም ከመብላት ይቆጠባሉ:: ስለዚህ ዓሣማ ከቤት ውጭ ከታሠረ እና ከተጠበቀ ሙስሊሞች ወደ ቤታችን ለጉብኝት ሲመጡ፣ ሲጫወቱና ሲወያዩ፣ እንዲሁም አብረው ምሣ ሲመገቡ እና ከጊዜ በኋላም እጅግ ድንቅ የሆነውን የወንጌል መልዕክት ይበልጥ ለመመልከት እና ለማዳመጥ ሲመርጡ ይችላሉ::

## 18. የበርናባስ ወንጌል እውነተኛው ወንጌል ነው

አዲስ ኪዳን ትክክለኛው ወንጌል አይደለም የሚሉ ሙስሊሞች «እውነተኛውን» ለማግኘት በከንቱ ምርመራ ለፍተዋል:: አንዳንድ ሙስሊሞች ሊያደርጉ የቻሉት መልካሙ ነገር የበርናባስ ወንጌል የተባለውን መጽሐፍ ማቅረብ ነበር:: ምናልባት ይህ ሥራ፣ የጥንት አማኝ በነበረው እና ሐዋርያው ጳውሎስን በመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉብኝቱ ላይ አጅቦት በነበረው በበርናባስ የተጻፈው እውነተኛ ወንጌል ሊሆን ይችላል:: /የሐዋ.ሥራ 31:1-4/:: ይሁን እንጂ ዘመናዊ የትምህርት አዋቂዎች «የበርናባስ ወንጌል» ስለሚባለው መጽሐፍ የሚናገሩት አላቸው:: ይኸውም፣

> «በበርካታ የጥንት ፀሐፊዎች፣ በተለይም በ«ጋላሲየስ ውሳኔና ትእዛዝ» (በ500 ዓ.ም) የተጠቀሰ የ«በርናባስ ወንጌል» የሚባል መጽሐፍ ነበር፣ ነገር ግን ስለመልዕክቱ ይዘትና ፍሬ ነገር ወይም ባህርይው የተገለፀ ነገር

የለም። ይሁን እንጂ በዚሁ ርዕስ ስር ከሙስሊም አስተሳሰብ እና አቋም አንፃር የተፃፈ እና ጠንካራ የግኖስቲሲዝም ዋና ባህሪ የያዘ የጥንት የኢጣሊያን ጽሑፍ ይገኛል። ጽሑፉ በ13ኛው እና በ16ኛው ክ/ዘመን መካከል ባለው አንድ ወቅት ላይ *ከክርስትና ኃይማኖት አፈንግጦ የወጣ ሰው የሠራው ሥራ ነው» ብለው ባመኑት* በሎንስዴል እና ላውራ /ኤም ሮበርትስ/ ራግ በ1899 ዓ.ም የተዘጋጀ ነው። ልክ እንደ አብዛኞቹ ከቤተክርስቲያን አባቶች ፅሁፍ ጋር እንደተያያዙ እና የመሐከለኛው ዘመን የማይታመን ፅሁፍ እንደሆኑት፣ ይህም ሥራ በከፍተኛ ሁኔታ በምናብ የተፈጠረና ከታሪካዊ ባህልና ልምድ ይልቅ የልብ ወለድ ሥራ የሆነ፣ ነገር ግን ጥብቅ እና ጠንካራ የሆኑ የሥነ ምግባር ሥረ-ነገሮች /ኤምፈሲስ/ ያለበት ነው» የሚል ነበር።

ኢንሳይክሎፒዲያ አሜሪካና
የ1968 ዓ.ም ዕትም፣ገጽ 247

ነገር ግን ከዚሁ የበርናባስ ወንጌል መጽሐፍ አጠራጣሪ ባህርይ የተነሳ፣ መጽሐፉን በቁም ነገር የወሰዱት ጥቂት ሙስሊሞች ብቻ ናቸው። እነዚህም የክርስትና ኃይማኖት እና መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥቃት ያዘነበሉ ናቸው።

በጣም የተማሩት እና የቁርአንን ጥቅሶች በሚገባ ያወቁት እንዲሁም የፍልስጤምን ታሪክና መልክ ምድር የሚያውቁ ሙስሊሞች ግን ይህ ዓይነቱ መጽሐፍ መለኮታዊ ምንጭነት አለው ብለው መናገር ለኢስላም ዓላማና ጉዳይ በግልፅ አሳፋሪ መሆኑን ያውቃሉ። ምክንያቱም የበርናባስ ወንጌል ከቁርአንም ሆነ በኢየሱስ ዘመን ከነበረው የፍልስጤም ታሪካዊ መነሻ መደብ /ባክግራውንድ/ ጋር የሚቃረን ነው። እነዚህ ልዩነቶች ደግሞ በጥያቄ ምልክት ውስጥ ከሚገኘው ከዚሁ ጽሑፍ ጋር ከምሳሌዎች ጋር ሆነው በምድብ ተዘርዝረዋል።

## ሀ. የመሢሑ ማንነት

የዚህ መጽሐፍ /የበርናባስ ወንጌል፣ ዕትም 1899 ዓ.ም/ አበይት ዓላማዎች አንዱ «መሢህ» የሚለውን ማዕረግ ከኢየሱስ ወደ ነቢዩ መሐመድ ለማዛወር ነው። ይሁን እንጂ ይህ ሙከራ በውስጣዊ እና በውጫዊ መረጃዎች የተቃረነ ነው።

የሚከተሉት መግለጫዎች «መሢህ» የሚለውን ማዕረግ ከኢየሱስ ለመውሰድ ፀሐፊው ያደረገውን ሙከራ ያረጋግጣሉ።

- ገጽ 122፣ ምዕራፍ 96:- ኢየሱስ መሢህ እንዳልሆነ ተናግሯል፣ ይላል
- ገጽ 123፣ ምዕራፍ 97:- መሐመድ መሢህ ነኝ ብሎ ተናግሯል፣ ይላል
- ገጽ 182፣ ምዕራፍ 142፣- መሢሁ የዳዊት ወይም የይስሐቅ ዘር አይደለም፣ ይላል

ከበርናባስ ወንጌል ውስጥ የተገኙት የላይኞቹ መግለጫዎች ቢኖሩም እንኳ፣ ቁርአን ግን አል-መሢሀ /መሢሁ/ የሚለውን ማዕረግ ለማንም ሌላ ሰው ሣይሆን የማርያም ልጅ ለሆነው ለኢየሱስ በግልጽ ይሰጣል። ይህ ልዩ ማዕረግ በቁርአን ውስጥ መሐመድን ጨምሮ ለማንም ነቢይ አልተሰጠም። የሚከተሉትን ቁርአናዊ መግለጫዎች ያስተውሉ።

- የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሣ የአላህ መልክተኛ ወደ መርየም
- የጣላት (የኾን) ቃሉም ከእርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው።

ሱረቱ አል ኒሳእ /4/:171

መላእክት ያሉትን (አስታውስ):- መርየም ሆይ! አላህ ከእርሱ በኾነው ቃል ስሙ አልመሲሕ ዒሣ የመርየም ልጅ፣ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም አለም የተከበረ ከባለሟሎችም በሆነ (ልጅ) ያበስርሻል፣

ሱራቱ አሊ-ኢምራን /3/:45

በተጨማሪ መታወስ ያለበት ነጥብ፣ ሙስሊሞች ኢየሱስ ከአይሁድ ዝርያ መምጣቱን፣ የአብርሃም፣ የይስሐቅ እና የያዕቆብ ዝርያ ከሆነው ከነቢዩ ዳዊት የዘር ሐረግ መወለዱን በተመለከተ ከመጽሐፍ ቅዱስ ዕውነት ጋር ይስማማሉ። ቁርአን እራሱ ኢየሱስ መሢህ መሆኑን አረጋግጦ የሚገልጽ ስለሆነ «መሢሁ የዳዊት ወይም የይስሐቅ ዘር አይደለም» የሚለው የበርናባስ ወንጌል መግለጫ ከሙስሊም እምነት ጋር በግልጽ ይቃረናል።

በመላው የበርናባስ ወንጌል ውስጥ፣ ፀሐፊው «ክርስቶስ» የሚለውን፣ ማለትም የኢየሱስን የመሢህነት ማዕረግ የሚጠቀም ሲሆን፣ የዚያኑ ያህል ደግሞ ኢየሱስ መሢህ አይደለም ሲል ይከራከራል።

ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ትውፊታዊ ሁኔታዎች ትክክል አለመሆን

- ገጽ 5፣ ምዕራፍ 3፡ ማርያም ኢየሱስን የወለደችው ያለምንም የወሊድ ስቃይ ነው የሚል ነገር ተገልጿል:: ቁርአን ግን በግልጽ ሁኔታ በተለየ መንገድ ይናገራል::

> ወዲያውኑ አረገዘችው፣ በእርሱም (በሆዷ ይዛው) ወደሩቅ ስፍራ ገለል አለች:: ምጥ ወደ ዘንባባይቱ ግንድ አስጠጋት፣ ዋ ምኞቴ! ምነው ከዚህ በፊት በሞትኩ፣ ተረስቼም የቀረሁ በኾንሁ፣ አለች::
>
> ሱረቱ መርየም/19/ 22:23

ገጽ 26፣ ዕምራፍ 23፡ ግርዛት የተጀመረው በአዳም ነው ተብሏል:: ይሁን እንጂ፣ ይህ ዓይነቱ የግርዛት ሥርዓት የተጀመረው በአብርሃም እና እስማኤል ማህበረሰብ ውስጥ እንደሆነ የሙስሊም ትውፊታዊ ባህልም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል::

ገጽ 46፣ ምዕራፍ 35፡ የሰው እምብርት የተሠራው ከሰይጣን ለሀጭ እንደሆነ ተነግሯል:: ነገር ግን ፀሐፊው በገጽ 50፣ ምዕራፍ 39 ላይ ውሻ የተፈጠረው ከሰይጣን ለሀጭ ነበር፣ ይላል:: ነገር ግን ቁርአንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን እምብርት ጨምሮ በሰው አካል አፈጣጠር ውስጥ ሰይጣን በፍፁም ድረሻ ነበረው ሲል አያመለክትም:: ከዚህ በተጨማሪ ኃያሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ማንኛውንም የሰው አካል ሲፈጥር የሰይጣን እርዳታ እንዳላስፈለገው አብዛኞቹ ሙስሊሞች ይስማማሉ::

ገጽ 51፣ ምዕራፍ 39፡ አዳም እና ሔዋን ዕፀ በለሶቹን እና በቆሎውን እንዳይበሉ ተከልክለው ነበር ይላል:: ቁርአን ግን የሚከተለውን ይተርካል::

ሱረቱ አሊ-ኢምራን/3/:55

እርግጥ ነው፣ በተከለከለው ዛፍ ላይ «ዕፀ በለሶች» በደምብ ሊኖሩ ይችላሉ:: «በቆሎ» ግን በዛፎች ላይ እንደማይበቅል በሚገባ የታወቀ ነው::

- ገጽ 57፣ ምዕራፍ 44፡ ለይስሐቅ ዝርያ የተገባለት ቃል ኪዳን ወይም የተሰጠው የተስፋ ቃል ሃሳብ ስህተት ነው ተብሏል:: ይሁን እንጂ፣ በቁርአን የትኛውም ክፍል ውስጥ ከእስማኤል ወይም ከዘሮቹ ጋር ስለተደረገ ቃል ኪዳን በፍፁም አይጠቅስም:: ለእንዲህ

ዓይነት የተስፋ ቃል ወይም ቃል ኪዳን የተደረጉ መግለጫዎች ሁሉ የይስሐቅን ዘር፣ ይኸውም እስራኤልን /ያዕቆብን/ እና ዝርያዎቹን የሚመለከቱ ናቸው::

- የእስራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋዬን አስታውሱ፣ በቃል ኪዳኔም ሙሉ፣ በቃል ኪዳናችሁ እሞላለሁና፣ እኔንም ብቻ ፍሩ::

ሱረቱ አል-በቀራህ /2/:40

- ገጽ 132፣ ምዕራፍ 105: ስለ «ዘጠኝ» ሰማየ ሰማያት የተገለፀ ቢኖርም ቁርአን የሚናገረው ስለ «ሰባት» ሰማያት ብቻ ነው:: ይኸውም:-

ከዚያም ወደ ሰማይ አሰበ፣ ሰባት ሰማያትም አደረጋቸው ....፣ ይላል

ሱረቱ አል-በቀራህ /2:29/

- ገጽ 134፣ ምዕራፍ 106: «ገሃነም» ሊቋቋሙት የማይቻል ቀዝቃዛ ውኃና አመዳይ በረዶ ያለበት ሥፍራ ተደርጐ ተገልጿል:: አብዛኞቹ የቁርአን መግለጫዎች ግን ገሃነምን የሚፋጅ ነበልባል እና የሚፍለቀለቅ ውሃ ያለበት ሥፍራ አድርገው ይገልፁታል::

- ገጽ 141፣ ምዕራፍ 112: ኢየሱስ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ወደ መንግስተ ሰማይ አልነሳም ብሏል፣ ተብሎ ተገልጿል:: የሚከተሉት የቁርአን መግለጫዎች ግን በሌላ በኩል ይገልጻሉ:: ይኸውም:-

አላህም ባለ ጊዜ (አስታውስ)፣ ዒሣ ሆይ! እኔ ወሳጅህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ ...፣ ይላል::

ሱረቱ አሊ-ኢምራን /3/:55

ይልቁንስ አላህ ወደርሱ አነሳው፣ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፣ ይላል

ሱረቱ-አል ኒሳእ /4/:158

- ገጽ 156፣ ምዕራፍ 124: «መዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ /ዛቡር/ የተሰጠው በሙሴ መጻሕፍት /ታውራት/ ውስጥ የተሳሳተ ሃሣብ ስለነበር ነው፣ አዲስ ኪዳን /ኢንጂል/ የተሰጠውም በመዝሙረ ዳዊት /ዛቡር/ ውስጥ ከጊዜ በኋላ በተጓዳኝ የተከሰተ ስህተትና ጉድለት በመኖሩ ነው፣ ተብሎ ተገልጿል::

ይህ ዓይነቱ የአስተሳሰብና የመመራመር መስመር ግን በቁርአን ውስጥ የለም። በተቃራኒው መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ዘር ሁሉ የሚሆን ብርሃን እና መሪ ተደርጎ ተገልጿል። መጽሐፍ ቅዱስ ጉድለት ቢኖርበት ኖሮ፣ ቁርአን የሚከተሉትን ተግሳፅና ማስጠንቀቂያዎች በውስጡ አይዝም ነበር። ይኸውም፡-

> እነሱም ተውራትንና ኢንጂልን ከጌታቸውም ወደ እነርሱ የተወረደውን መጽሐፍ ባቋቋሙ (በሰሩበት) ኖሮ ከእግሮቻቸው ስር በተመገቡ ነበር።
>
> ሱረቱ አል ማኢዳህ /5/:66

> እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ፣ በአላህና በመላእክቱም በመጽሐፎቹም በመልክተኞቹም በመጨረሻውም ቀን የካደ ሰው (ከውነት) የራቀን መሳሳቅ በርግጥ ተሳሳተ።
>
> ሱረቱ-አል ኒሳህ 4:136

- ገጽ 273 ምዕራፍ 221፡ ኢየሱስ «አልሞትኩም» ብሎ ተናግሯል ተብሎ ተጠቅሷል። ነገር ግን አብዛኞቹ ሙስሊሞች የኢየሱስን መሞት ቢክዱም እንኳ ቁርአን ግን ስለዚህ ጉዳይ ግልጽ ያልሆነ ሲሆን ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር ከማረጉ በፊት ሞቶ እንደነበር ለማመን የሚያስችል ጠንካራ ማስረጃ ግን ጨምሮ ይሰጣል።

> አላህም ባለ ጊዜ (አስታውስ)፣ ዒሣ ሆይ! እኔ ወሳጅህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ ...፣ ይላል።
>
> ሱረቱ አሊ-ኢምራን /3/:55

«እወስድሃለሁ» የሚለው የአረብኛ ቃል አገላለጽ «እንድትሞት አደርግሃለሁ» የሚል ትርጉም አለው። ይህ አገላለጽ በድጋሚ በሱረቱ አል ማይዳ /5/:117 ውስጥ የተገለፀ ሲሆን፣ እዚህ ላይ ኢየሱስ ራሱ «መቼ ትወስደኛለህ» ብሎ ለእግዚአብሔር የተናገረበት ይገኛል። እዚህ ላይ በድጋሚ የአረብኛው ቃል «መቼ ትገድለኛለህ» የሚል የቁም ትርጉም አለው።

በተጨማሪም ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር ከመሄዱ በፊት ሞቶ እንደነበር የሚያሳይ ሌላ ጥቅስ አለ። ለምሳሌ ያህል እንዲህ እንዳለ ተደርጎ ተጠቅሷል።

> ሰላምም በእኔ ላይ ነው በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን ህያው ሆኜ በምቀሰቀስበትም ቀን፤
>
> ሱረቱ መሪየም /19/:33

በቅዱስ ቁርአን ትርጉሜ ላይ፣ ኤ-ዩሱፍ አሊ የሚባል ግለሰብ በግርጌ ማስታወሻው ቁጥር 2485 ላይ «ኢየሱስ አልሞተም ብለው የሚያምኑ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ አጥብቀው ማሰብ ይኖርባቸዋል» ብሏል። አብዛኞቹ ሙስሊሞች ከዚህ ጉዳይ ለማምለጥ ሲሉ፣ ኢየሱስ የሚሞተው ወደ ምድር በሚመለስ ወቅት ነው በማለት ያስተምራሉ። ይህ ዓይነቱ ትምህርት ግን በቁርአን ውስጥ አይገኝም።

በበርናባስ ወንጌል ውስጥ ሙስሊሞች ያህያ ብለው ብለው ስለሚጠሩት መጥምቁ ዮሐንስ ምንም የተገለፀ ነገር አለመኖሩን ማስተዋልም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ በቁርአንም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታዋቂ እና ስመ ጥር ሰው ነው። የኢየሱስን መምጣት ለማብሰር እና መንገድ ለመጥረግ ልዩ ሥራ የተሰጠው ነበር። የዮሐንስ ቀዳሚ ተልዕኮ ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተቀባ «መሢሕ» መሆኑን ማረጋገጥ ነበር። አሁን ግን የበርናባስ ወንጌል ፀሐፊ ለምን ሙሉ በሙሉ የመጥምቁ ዮሐንስን መግለጫ እንደዘለለው ግልጽ ሆኗል። ይኸውም መሐመድን መሢሕ ለማድረግ በሞከረው ሙከራ ውስጥ፣ ኢየሱስን የመሢሁ መስካሪ በማድረግ የመጥምቁ ዮሐንስን ተልዕኮ አስፈላጊነት ለማጥፋት ነበር። ይህ ሁሉ ግን ከቁርአን ትምህርት ጋር የሚቃረን መሆኑ ግልጽ መሆን አለበት!

### ሐ. የመልክአ ምድራዊ እና ታሪካዊ ሁኔታዎች ትክክለኛ አለመሆን

ገጽ 22 ምዕራፍ 20: «ኢየሱስም... በመርከብ ላይ ተሳፍሮ ወደ ናዝሬት ከተማው ሄደ» ይላል። እዚህ ላይ የናዝሬት ከተማ በተገለፀችው ሁኔታ የባህር ወደብ ሳትሆን በመሃል ሀገር እንደምትገኝ ተደርጎ ተገልጿል።

ገጽ 23 ምዕራፍ 21: «ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም ሄደ» ተብሎ ተገልጿል። ይሁን እንጂ ቅፍርናሆም በመሃል ሀገር ውስጥ የምትገኝ ሳይሆን፣ በገሊላ ባህር ዳርቻ የምትገኝ የወደብ ከተማ ናት።

- ገጽ 116 ምዕራፍ 92: «ኢየሱስ ወደ ሲና ተራራ እንደተጓዘ እና ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ እንደተጠጋ» ተገልጿል:: ይሁን እንጂ የሲና ተራራ የሚገኘው እስራኤልን ከግብፅ በሚያዋስነው አቅጣጫ ሲሆን፣ የዮርዳኖስ ወንዝ ደግሞ እስራኤልን ከዮርዳኖስ ጋር በሚያዋስነው አቅጣጫ ነው፣ በመሆኑም እነዚህ ሁለት አካባቢዎች እጅግ በጣም የሚራራቁ እንጂ በፍፁም ቅርብ አይደሉም::

- ገጽ 217 ምዕራፍ 196: «ሁሉም ነገር የሚያፈራበት የክረምት ወቅት እንዴት ውብ ነው» የሚል ተገልጿል:: ይህ መግለጫ ግን እንደ አውሮፓ ላሉ ክፍሎች እውነት ቢሆንም የፍልስጥኤም የበጋ ወራት ግን በሚያቃጥል እና በሚለበልብ ፀሀይ ሁሉም ነገር ደርቆ መካን ስለሚሆን መግለጫው ለፍልስጥኤም አይሆንም::

- ገጽ 4 ምዕራፍ 3: «ኢየሱስ የተወለደው አናንያና ቀያፋ ካህን በነበሩበት የጲላጦስ የግዛት ዘመን ነው» የሚል ተገልጿል:: ይሁን እንጂ ጲላጦስ እስከ 26-27 ዓ.ም ድረስ ገዥ እንዳልነበር ታሪክ መዝግቧል::

- ገጽ 11 የምዕራፍ 12: በዚህ ላይ የተጠቀሱት እና «ወደ ከፍታ መውጣት» የሚሉት ቃላት በይበልጥ የሚያመለክቱት በ15ኛው በ16ኛው ክ/ዘመናት ላይ በአውሮፖ ውስጥ ከከፍተኛ ሠገነቶች ላይ ይሰጡ የነበሩትን የንግግር መልዕክቶች ነው:: ይህ የተለየ አገላለጽ ግን የፍልስጥኤም አይሁዶች ከምኩራቦቻቸው የሚሰጧቸውን የስብከት አሰጣጥ ዘዴዎች አይገልፁም::

- ገጽ 19 ምዕራፍ 18: ኤልዛቤል 10.000 ነቢያትን አርዳ እንደገደለች ተገልጿል:: ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በታሪክ ገጾች ውስጥ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ አልተመዘገበም::

- ገጽ 41 ምዕራፍ 32: የበዓል ጣዖት አምልኮ በዓለም ላይ ሁሉ እንደተስፋፋ ተገልጿል:: ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱን ንግግር በማስረጃ የሚደግፍ ምንም የሥነ ቅሪት /አርኪዮሎጂካል/ ማስረጃ የለም::

- ገጽ 82 ምዕራፍ 65: ፕሮባቲካ የሚለው ቃል ኩሬን አስመልክቶ ተጠቅሷል:: ይሁን እንጂ ይህ ቃል የግሪክ ስም የነበረ እና «የበጐች በር» የሚባለው አንዱ የእየሩሳሌም ከተማ መግቢያ በር ነበር::



74

- ገጽ 115 ምዕራፍ 91: 600.000 የሮማ ወታደሮች በትንሿ የሚፅፋ ከተማ ውስጥ መሰብሰባቸው ተገልጿል:: ይህ ዓይነቱ ድርጊት ግን በሮም የታሪክና የክስተት መዛግብት ውስጥ ያልተመዘገበ በመሆኑ ፍፁም የተጋነነ ነው!

- ገጽ 130 ምዕራፍ 103: ምንም እንኳ «መርከበኛ» እና «መርከብ» የሚል ቃላት በጽሑፉ ውስጥ ቢገኙም እነዚህ ቃላት ግን ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን እና ሥፍራ ለፍልስጥኤሞች የተለመዱ ሳይሆን በይበልጥ በመሐከለኛው ዘመን የነበሩትን ስፔን እና አጣሊያ የሚያመለክቱ ናቸው::

- ገጽ 185 ምዕራፍ 145: በነቢዩ ኤልያስ ጊዜ ስለነበሩ 17.000 ፈሪሳውያን የተገለፀ ነገር አለ:: ይሁን እንጂ በአይሁዳውያን የማካቢያን ዘመን እስከ 200 ዓመተ ዓለም ድረስ የፈሪሳውያን የእምነት ወገን አልተፈጠረም ነበር:: ኤልያስ የኖረው ከዚያ ጊዜ 700 ዓመታት በፊት በ900 ዓመተ ዓለም ነበር::

- ገጽ 196 ምዕራፍ 152: ወታደሮች የወይን ጠጅ መሙያ በርሜል በሚታጠብ ጊዜ እንደ እንጨት በርሜሎች ይንደባለሉ እንደነበር ተገልጿል:: ይሁን እንጂ በኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን የእንጨት በርሜሎች የተለመዱ አልነበሩም:: በዚያን ጊዜም ሆነ እስካሁን ድረስ ለወይን ጠጅ መያዥ የሚጠቀመው ከእንስሳት ቆዳ የሚሰራ አቁማዳ እንጂ እንጨት አልነበረም:: የእንጨት የወይን በርሜሎች የሚገልፁት የመሐከለኛውን ዘመን አውሮፖ ሲሆን፣ ወደሌላው ዓለም የተላኩትም ከዚያው ነው::

- ገጽ 262 ምዕራፍ 214: ስለ 30 የወርቅ ሣንቲሞች ተገልጿል:: ነገር ግን በኢየሱስ ዘመን የፍልስጥኤም የገንዘብ ዓይነት የብር /ሲልቨር/ ሣንቲሞች ነበሩ::

መደምደሚያ:- ከአብዛኞቹ ከተሰጡት ምሣሌዎች ስንመለከት ይህ የበርናባስ ወንጌል የሚባለው መጽሐፍ መለኮታዊ ምንጭነት እንደሌለው ለሙስሊሞችም ሆነ ለክርስቲያኖች ግልጽ መሆን አለበት:: ሁሉም ማስረጃ የሚያሳየው በተለይ በአውሮፓ የመሐከለኛው ዘመን ላይ የክርስትና ኃይማኖትን ለማጥቃት በአንድ ሰው የተቀነባበረ ማጭበርበሪያ መሆኑን ነው:: የበርናባስ ወንጌል የተጻፈው የእስላሞች በክርስቲያኖች ከስፔን መባረር ባናደደው እና መሐመድን ከኢየሱስ አስበልጦ ለማቅረብ በሞከረ ግለሰብ እንደሆነ አንዳንድ ተመራማሪዎች ያስባሉ:: ይህ ዓይነቱ የማይታመን ሥራ ግን በእውነት ፈላጊዎች መጋለጡ ግልጽ ነው:: ምክንያቱም እውነት ለዘላለም ያሸንፋልና!

# ተጨማሪ አባሪዎች

## ኢስላማዊ ቃላት/ስሞች/አገላለፆች

1. ለሰላምታ:- ሰላም ለአንተ ይሁን - አስ ሰላሙ አላይኩም
   መልሱ:- ለአንተም ሰላም ይሁን - ዋአለይኩም አስ ሰላም
2. እግዚአብሔር:- አላህ /አል-ኢላህ /
3. ታላቁ እግዚአብሔር:- አላህ ጣአል
4. የከበረውና እና የተወደሰው እግዚአብሔር:- አላህ ሱብሃን ዋ ጣአል ወይም አላህ
5. እግዚአብሔር ታላቅ ነው:- አላህ አክበር
6. በእግዚአብሔር ስም:- ቢስሚላህ
7. በቸሩ እና በሩህሩሁ እግዚአብሔር ስም :- ቢስሚላህ አር ረህማን - አር ራሂም
8. እግዚአብሔር ይመስገን /ሀሌሉያ/:- አል ሃምዱሊላህ
9. የሰማይና የምድር ጌታ /የዓለም ጌታ/:- ራብ-ኡል አለሚን
10. መሢሕ ኢየሱስ - ኢሣ አል-መሢሕ
11. አብርሃም - ኢብራሂም
12. ይስሐቅ እና ያዕቆብ - ኢሻቅ እና ያቁብ
13. እስማኤል - እስማኤል
14. ሙሴ እና አሮን - ሙሳ እና ሃሩን
15. ዳዊት እና ሰለሞን - ዳውድ እና ሱሌይማን
16. መጥምቁ ዮሐንስ - ያህያ
17. ነብይ - ነቢ
18. ማርያም -መሪማ
19. ገብርኤል /የመንፈስ ቅዱስ መልዕክተኛ/ ጂብሪል ወይም ሩህ ኡል ቅዱስ
20. መሐመድ - መሐመድ
21. መጽሐፍ ቅዱስ - አልኪታብ - ኡል ሙቃዳስ
22. የሙሴ መጻሕፍት /ቶራህ/ - አል -ታውራት
23. መዝሙረ ዳዊት - አልዛቡር
24. አዲስ ኪዳን /ወንጌል/ - ኢንጂል /ሻሪፍ/
25. የነቢያት ጽሑፎች - ሱሁፍ - ኡን ነቢይን
26. ኢየሩሳሌም -አል ቁድስ
27. ኢስላማዊ የሃይማኖት ሕግ - ሽሪዓ

## በመጽሐፍ ቅዱስ እና በሙስሊም ባህሎች መካከል ያሉ መመሳሰሎች

## የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይማኖት ልማዶች

1. ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን - ሉቃስ 10:5
2. ከአምልኮ በፊት እጅና እግርን መታጠብ - ኦሪት ዘፀዓት 40:31-32
3. ጫማዎችን ማውለቅ - ኦሪት ዘፀዓት 3:5
4. በንፅህና ለፀሎት መስገድ - መዝሙር 95:6
5. የእንስሳት መስዋዕት /ፋሲካ/ - ኦሪት ዘዳግም 16:1-6
6. ወደ ኢየሩሳሌም የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ - የሐዋ.ሥራ 8:26-28
7. በአምልኮ ጊዜ የሴቶች ፀጉር መሸፈን - 1ኛ ቆሮ 11:5-6
8. ግርዛት - ሉቃሴ 2:21
9. ለበኩር ልጅ መስዋዕት ስለማቅረብ - ሉቃስ 2:24
10. የረዥም ጊዜ ጾም - ዘፀ.34:28 1ኛ ነገሥት 19:8፣ ማቴ 4:2
11. የዓሣማ ሥጋ አለመብላት - ዘሌዋውያን 11:7

## የሙስሊም ልምዶች

1. ሰላምታ - አስ-ሰላሙ አለይኩም /ሰላም ለአንተ ይሁን/
2. ለሃይማኖታዊ ሥርዓት መታጠብና እና መንፃት - ውዱ
3. በመስጊድ ውስጥ ጫማ አይደረግም
4. በፀሎት ጊዜ የሚደረግ ንፅህና - ሳጅዳ
5. የእንስሳት መሰዋዕት በዓል - ኢድ አልአድሃ /ኢድ-አል ቁርባን
6. ወደመካ የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ - ሐጅ
7. ሴቶች የሚለብሱት የራስ መሸፈኛ ጨርቅ
8. ግርዛት - ኪታን
9. ሕፃን ልጅ ሲወለድ የሚቀርብ መስዋዕት - አኪካ
10. በረመዳን ጊዜ የሚኖር የ30 ቀናት ጾም - ጾም
11. ሙስሊሞች የዓሣማ ሥጋ ከመብላት ይቆጠባሉ::